
# የኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት ጦስና ትኩረት ያጣው በድንበር አካባቢ የሚኖር የትግራይና የዓፋር ህዝብ መከራ

***በተለይ የድንበሩ አዋሳኝ በሆኑት  የትግራይና አፋር ወረዳዎች በአጭር ጊዜ የተደረገ ዳሰሳና የችግሮቹ አመላካች ፅሁፍ***







ሰኔ 2010

አዲስ አበባ



# ርእስ

## የኢትዮጵያና ኤርትራ ጦርነት ጦስ እና ትኩረት ያጣው በድንበር አከባቢ የሚኖር የትግራይና የዓፋር ህዝብ መከራ

(በተለይ የድንበሩ አዋሳኝ በሆኑት የትግራይ አከባቢዎች በተደረገ ዳሰሳ መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ጥናታዊ ፅሁፍ)

## አዘጋጅ

ሌ/ጀነራል ዮሀንስ ገብረመስቀል

ረዳት አቶ አክሊሉ ደባልቀው

## ጥናቱ የተዘጋጀበት ጊዜ

ሰኔ 2010 ዓ/ም

## ምስጋና

የጥናቱ ሙሉ ወጪ በአዘጋጁ የተሸፈነ ሲሆን የትግራይ ክልል ላቀረበልን የትራንስፖርር አገልግሎት እና ሌሎች ትብብሮች በተለይ ደግሞ ከክልል እስከ ወረዳ ያሉ የፀጥታ አካላት ላደረጉልን ትብብር ምስጋናችን የላቀ ነው።

## *የባለቤቱ መብት በህግ © የተጠበቀ ነው*

## መውጫ

1. መግቢያ ........ 3
2. ነባራዊ ሁኔታ ........ 3
3. የጥናቱ ዓላማ ........ 5
4. የጥናቱ ወሰን ........ 6
5. የአጠናን ዘዴ እና የመረጃ ምንጭ ........ 6
6. ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው አከባቢዎች አጠቃላይ መረጃ ........ 6
 6.1. ትግራይ ........ 6
 6.2. ዓፋር ........ 7
7. የችግሩ አጀማመር እና አንኳር ሂደቶች ........ 8
8. የሀያ አመቱ የጦርነት ቀጠናው ሁኔታ እና ህዝቡ ........ 13
 8.1. በትግራይ በኩል የሚገኘው በጦርነቱ ጊዜና ከዛ በኃላ ተጠቂ የሆነው ቀጠና ........ 13
 8.2. በዓፋር በኩል የሚገኘው በጦርነቱ ጊዜና ከዛ በኃላ ተጠቂ የሆነ ቀጠና ........ 16
9. ህዝቡ እና የሁለቱ ሀገሮች የሰራዊት አሰፋፈር ........ 18
10. የምልሻ ተሳትፎና ተግዳሮቶቹ ........ 23
11. የአካባቢው ኗሪ ህዝብ አስከፊ ኑሮ ........ 29
 11.1. ኢኮኖሚያዊ ........ 34
 11.2. ማሕበራዊ ........ 42
 11.3. ስነልበናዊ ........ 44
 11.4. ፖለቲካው ........ 45
12. የፌደራል እና የክልሎቹ መንግስታት ችግሩን ለመፍታት ያደረጉት እንቅስቃሴ ........ 51
13. አጭር ማጠቃለያና የመፍትሄ አቅጣጫ ........ 54

## 1. መግቢያ

ይህ ፅሁፍ በ1990 ዓ/ም የተጀመረው የኢትዮጵያና ኤርትራ የድንበር ጦርነት እና ለአስራ ስምንት ዓመት የዘለቀው ያልተነገረለት ቀዝቃዛ ጦርነት በሁለቱም ሀገሮች ድንበር በሚኖሩት የትግራይ እና ዓፋር ህዝቦች ላይ ያሳደረው ተፅእኖን ለመዳሰስ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ፅሁፍ ነው።

ለጥናቱ መነሻ የሆነው ነባራዊ ሁኔታ፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴ እና የጥናቱ ግኝትን በማካተተት ተዘጋጅቷል።

## 2. ነባራዊ ሁኔታ

የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለዘመናት ኢትዮጵያን ለማጥቃት በሚመጡ ሀይሎች እና ወራሪዎች ቅድምያ ተጠቂ ነው፡፡ የወራሪዎች ጥቃት ሰለባ ብቻም ሳይሆን ጥቃትን በማስቆም እና በመመከት ረገድም ቢሆን ምትክ የሌለው አኩሪ ተግባር መስራቱ የታሪክ እውነታ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል አጥር የሆኑት የትግራይ እና የዓፋር ክልሎች ላይ የሚደርሰው መከራ ከፍተኛ ነው፡፡ የነዚህ የሀገራችን አከባቢ ነዋሪ ህዝብ ሀገራችን በየግዜው የገጠምዋትን ጦርነቶች በመመከት ረገድ የፊት ሀይል በመሆን ለመላው የሀገራችን ህዝቦች ዘብ መሆን ብቻ ሳይሆን በሚደርስ ጥቃት እና ጥፋት ዋና ተጠቂም ነው፡፡ በየግዜው በአከባቢው በሚደረጉ ጦርነቶች ከሚደርስበት ግድያ እና የጅምላ ጭፍጨፋ በተጨማሪ የሀብትና ንብረት ውድመት ሰለባም ነው፡፡ አከባቢው የጦርነት ቀጠና በመሆኑም በሰላም የመኖር፣ ሰርቶ የመልማት እና የማደግ ህልሙ ሲደናቀፍበት የኖረ ህዝብና አከባቢ ነው፡፡

ሌላ ቀርቶ ሀገራችን አሁን ለደረሰችበት ምእራፍ እንድትደርስ ያስቻለው እና ለ አስራ ሰባት አመታት የተደረገው የትጥቅ ትግል አብዛኛው የተካሄደው በዚሁ የሀገራችን ሰሜናዊ ክፍል ላይ ነው፡፡ አከባቢው ለ 17 አመታት የጦርነት ቀጠና ሆኖ ከቆየ በኃላ ከ1983 እስከ 1990 ዓ/ም ድረስ አንፃራዊ ሰላም የሰፈነበት ሁኔታ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ በድንበር ይገባኛል ምክንያት የኤርትራ መንግስት በለኮሰው እና ለሁለት አመታት የተካሄደውን ጦርነት ተከትሎ እስከአሁን ድረስ የዘለቀው ብዙ ያልተነገረለት የቀዝቃዛ ጦርነት ምክንያት አከባበቢው የተረሳ እና ትኩረት ያጣ የጦርነት ቀጠና ከሆነ እንሆ 20 አመት ሞልቶታል፡፡

ይህ አከባቢውን የጦርነት ቀጠና ያደረገው የኢትዮጵያ እና የኤርትራ ግጭት በተለይ የሁለቱም ሀገሮች አዋሳኝ በሆኑት የትግራይ እና የዓፋር ህዝቦችን የችግሩ ተሸካሚ እንዲሆኑ ያደረገ ጉዳይ ነው፡፡

በዚሁ ለ20 አመታት የጦርነት ቀጠና ሆኖ በቆየው የሀገራችን ክፍል ከኤርትራ ጋር አዋሳኝ በሆነው የትግራይ እና የዓፋር አከባቢዎች ብቻ በድምሩ ወደ ሁለት ሚልየን የሚጠጋ ህዝብ ይኖራል፡፡ ይህ ህዝብ በሁለቱም ሀገሮች የተካሄደው የሁለት አመት ጦርነት ወቅት ለከፍተኛ ውድመት፣ ሞት፣ ጉዳት እና ስደት ተዳርጓል፡፡ በሁለቱ የጦርነት ዓመታት ብቻ ከነዚህ አከባቢዎች ከግማሽ ሚልየን በላይ ህዝብ ቀያቸውን ጥለው ተፈናቅለዋል፡፡ ብዙ ሂይወት ጠፍቷል፣ ሀብትና ንብረታቸው ወድሟል፣ ተዘርፏል፡፡

ጦርነቱ በይፋ ካበቃ በኃላ ባሉት 18 አመታትም በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የነዚህ አከባቢዎች ህዝብ በሁለቱ ሀገር የጦር ሀይሎች ፍጥጫ ስር ተቀርቅሮ እየማቀቀ እንዲኖር የተገደደበት፣ በየቀኑ በሚያጋጥም የቶክስ ልውውጥ ሂወቱ እያጣ፣ የእንስሳ ሀብቱ እያጣ፣ ከልማት እና የአብዛኛው መተዳደርያ ከሆነው የግብርና ስራ ተስተጓጉሎ፣ በሚሰጠው እዚህ

ግባ የማይባል የስንዴ ምፅዋት በሂይወት እና ሞት ማህል በሰቆቃ እንዲኖር ተገዶ አማራጭ አጥቶ የኖረና ከባድ ችግር ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ነው፡፡

የዚህ መከራ እና ሲቃይ ሰለባ መሆኑ ሳያንሰው ደግሞ፣ የሀገሪቱም ይሁን የሁለቱም ክልሎች መንግስት ትኩረት አጥቶ እና ተረስቶ፣ ማግኘት የነበረበትን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ ጥቅም እና ድጋፍ ከማጣቱም በላይ፣ ድምፁን የሚያሰማበት መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችንም ጭምር ተነጥቆ፣ በልማት ወደኋላ እንዲቀር እና በሰላም፣ መረጋጋት እና ፀጥታ እጦት በከፍተኛ የአእምሮ እና ስነልቦና ችግር ትራውማ (Trauma) ውስጥ ሆኖ እየኖረ ያለ ህዝብ ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተገለፁት ነባራዎ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ነው ታድያ የጥናት ቡድኑ ላለፉት 18 አመታት የጦርነት ቀጠና ሆኖ በቆየው የትግራይ እና የዓፋር ክልል ህዝቦች ችግሩን ተሸክመዉትና፣ ከፍተኛ ጉዳት እያስተናገዱ እንደቆዩ እና እንዳሉ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ሁኔታውን ለመዳሰስ ጥረት የተደረገው፡፡

## 3. የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ ከ1990 ዓ/ም ጀምሮ ለሁለት አመታት የተካሄደው የኢትዮጵና የኤርትራ ጦርነትና ከዝያም ቀጥሎ ለ18 ዓመታት የዘለቀው በአካባቢው ብዙ ጉዳት ያስከተለውን ቀዝቃዛ ጦርነት በሁለቱም ሀገሮች ድንበር በሚገኙ የትግራይ እና ዓፋር ክልል ህዝቦች የሳደረው ተፅእኖ ለመዳሰስ እና የመፍትሄ ሀሳብ ለማስቀመጥ ነው።

## 4. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የኤርትራ አዋሳኝ በሁኑትና በጦርነቱ በቀጥታ ተጠቂ በሆኑት የትግራይ እና የዓፋር ክልል ህዝብ እና አከባቢ የሚያቶኩር ነው። በነዚህ ሁለት ክልሎች የተደረገው ዳሰሳም በክልሎቹ በተለይም ከኤርትራ ጋር በቀጥታ በሚዋሰኑት ዞኖችና ወረዳዎች ላይ በማተኮር የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ነው።

## 5. የአጠናን ዘዴ እና የመረጃ ምንጭ

ጥናቱ ዋና የመረጃ ምንጭ አድርጎ የተጠቀመው የጦርነቱ ቀጠና ውስጥ የሚኖሩና በተለይም በቀጥታ ከኤርትራ ጋር በሚዋሰኑ የትግራይ ወረዳዎች በኣካል በመገኘት የተደረገ ቅኝትን፣ የአከባቢው ነዋሪዎች፣ የአስተዳደር አካላት፣ የክልሉ የምልሻና የፀጥታ ሀይል ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ወይም ስለሁኔታው የሚያውቁ ወይም የሚጠቅሱ ምንጮችም ጥቅም ላይ ውሏል።

## 6. ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው አከባቢዎች አጠቃላይ መረጃ

ይህ ጥናት እና የጥናት ውጤት በኢትዮጵያ እና ኤርትራ አዋሳኝ በሆኑት እና በጦርነት ቀጠናው ውስጥ የሚገኙት የትግራይ እና ዓፋር ክልል ትኩረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

### 6.1. ትግራይ

የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜናዊው የኢትዮጵያ ጫፍ የሚገኝ ሲሆን ክልሉ በሰሜን ከኤርትራ፣ በምስራቅ ከዓፋር ክልል፣ በደቡብ ከአማራ ክልል እንዲሁም በምእራብ ከሱዳን ሪፐብሊክ ጋር የሚዋሰን ክልል ነው፡፡ የክልሉ መንግስት በ5 አሰተዳደራዊ ዞኖች፣ በአንድ ልዩ ዞን፣ በ35 ወረዳዎች እና በ74 ከተማዎች የተዋቀረ ነው፡፡ መቀሌን የክልሉ

መንግስት ርእሰ ከተማ ያደረገው የትግራይ ክልል 80,000 ስኩ.ኪ.ሜ የሚገመት የቆዳ ስፋት ይሸፍናል፡፡

የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ባለስልጣን ትንበያ መሰረት የትግራይ ህዝብ ብዛት ሀምሌ 2009 ዓ/ም ላይ 5,247,005 ደርሷል፡፡

በክልሉ ከሚገኘው ህዝብ 83% የሚሆነው በግብርና ስራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡ ጤፍ፣ ስንዴ እና ገብስ ዋነኛ የክልሉ ምርቶች ናቸው፡፡ የክልሉ የኢኮኖሚ መሰረት የሆነው እርሻ ስራ በሺዎች የሚቆጠር እድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም አሁንም ድርስ በአብዛኛው ከኃላቀር እና ባህላዊ አሰራር አልተላቀቀም፡፡ በዚህም ላይ በክልሉ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ተጋላጭ በመሆኑ፣ ድርቅ እና ጦርነት፣ ለዘመናት ሲፈራረቅበት የቆየ በመሆኑ፣ የመሬት መሸርሸር፣ የደን መጨፍጨፍ እና ከመጠን በላይ የሆነ የግጦሽ መሬት አጠቃቀም የተጋለጠም ስለሆነ የክልሉን መሬት ተራቁቶ ዛፍ-አልባ ሜዳዎች፣ ኮረብታዎችና ተራሮች በመፍጠሩ ለከፍተኛ ችግር አጋልጦታል፡፡

## 6.2. ዓፋር

ሰመራን የክልሉ ርዕሰ ከተማ ያደረገው የዓፋር ብሔራዊ ክልል በሰሜን ምስራቅ ከኤርትራ፣ በሰሜን - ምዕራብ ከትግራይ ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ ከአማራ ክልል፣ በደቡብ ከኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ - ምስራቅ ከሶማሌ ክልል እንዲሁም በምስራቅ ከጂቡቲ ጋር ይዋሰናል፡፡ የዓፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 95,265.67 ስኩየር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት ይሸፍናል፡፡

ክልሉ በ5 ዞኖች እና አርጐባ ልዩ ወረዳን ጨምሮ በ32 ወረዳዎች እና በ370 ቀበሌዎች የተዋቀረ ሲሆን የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ባለስልጣን ሀምሌ 2009 ዓ/ም ባስቀመጠው ትንበያ መሰረት 1.8 ሚልየን ህዝብ አለው፡፡ ከነዚህም 89.5 ከመቶ የሚሆነው ህዝብ በገጠራማው የክልሉ ቦታዎች ይኖራል፡፡

በዓፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኘው ህዝብ 90 ከመቶ የሚሆነው አርብቶ አደር ሲሆን፤ ግመሎችን፣ የቀንድ ከብቶችን፣ ፍየልና በግ እንዲሁም አህያዎችን ያረባል፡፡ በክልሉ ጥጥ፣ በቆሎ፣ ባቄላ፣ ማሽላ፣ ፓፓዬ፣ ሙዝ እና ብርቱካን በስፋት ይመረታሉ፡፡ ጨው የማውጣት ስራም በክልሉ በስፋት ይከናወናል፡፡

## 7. የጦርነቱ አጀማመር እና አንኳር ሂደቶች

ሚያዚያ 28/1990 ዓ.ም. የተወሰኑ የኤርትራ የጦር ኃይል አባላት በሰሜን ኢትዮጵያ ጫፍ በትግራይ ክልል ሥር ወደሚገኘው የባድመ ከተማ ሳይፈቀድላቸው ከነትጥቃቸው ለመግባት

ሙከራ ማድረጋቸውና በዚህ አጋጣሚ፤ በቦታው የነበሩ የኢትዮጵያ ምልሻዎችና የፖሊስ አባላት ትጥቃቸውን አውርደው እንዲገቡ ቢጠይቋቸውም ፍቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ የመጀመርያው ግጭት መጀመሩ ብዙዎች ይስማሙበታል። የኤርትራ ጦር ከስድስት ቀን በኃላ በታንክና በከባድ መሣርያ ታግዞ ግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ/ም ባድመንና አከባቢውን ከተቆጣጠረ በኃላ አከታትሎም ኢትዮጵያ ወስዳብኛለች የሚላቸውን ቦታዎች ሁሉ አስመልሳለሁ በማለት በተለያዩ ግንባሮች ሰፊ ወታደራዊ ዘመቻ በማካሄድ በሰኔ ወር 1990 ዓ.ም. በትግራይ በኩል ዛላ አንበሳን፣ ዓይጋን፣ ጉሎ-መኽዳን፣ እንዲሁም ዓሊቴናንና በጠቅላላው ኢሮብን፣ በዓፋር አቅጣጫ የቡሬ አካባቢ

መሬቶችን በመቆጣጠሩ እና በወቅቱም የኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በይፋ ኤርትራ ወረራ መፈፀምዋ ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ ነበር ሁለቱ ሀገሮች ወደ ይፋዊ ጦርነት የገቡት።

የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በሀይል ከያዘቻቸው ቦታዎች ለቃ እንድትወጣ ሲጠይቅ የኤርትራ መንግስት በበኩሉ ጉዳዩ በነፃና ገለልተኛ አካል እንዲታይ ነበር ጥሪ ያቀረበው። ይህንን ተከትሎም የአሜሪካና ሩዋንዳ መንግሥታት በጥምረት ግጭቱ ለማርገብ ግንቦት 22 ቀን 1990 ዓ/ም የሰላም ሀሳብ አቅርበዋል። የሰላም ሀሳቡ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ቢሆንም በኤርትራ በኩል ግን የአመሪካና የሩዋንዳ የሰላም ሀሳብን ጨምሮ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እና የተባበሩት መንግስታት ተከታትለው ያቀረቡዋቸውን ጥሪዎችንም ጭምር መቀበል ባለ መቻሉ ነበር ግጭቱ ወደለየለት ጦርነት የተቀየረው።

በዚህ ለሁለት አመታት በተካሄደው ጦርነት የተለያዩ ምንጮች እነደሚጠቅሱት ከ 80 ሺ በላይ ሰዎች ሂወት ተቀጥፈዋል። ቦጦርነቱ ምክንያትም በበርካታ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ቤት ንብረታቸውን ጥለው ተሰደዋል፣ ተፈናቅለዋል፣ ንብረትም ወድሟል።

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀሉ ሶዎች ቁጥር በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ነው። የኢትዮጵያ መንግስት እአአ ህዳር 17 2000 ላይ ባወጣው መረጃ መሰረት ጦርነቱ በተጀመረ በአንድ ወር ብቻ አንድ መቶ ሰባ ሰባት ሺህ (177,000) ዜጎች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። በአጠቃላይ በሁለቱ የጦርነት አመታት አዋሳኝ ከሆኑት የትግራይ እና ዓፋር አከባቢዎች ሶስት መቶ ስድሳ ሺህ (360,000) ሰዎች ተፈናቅለዋል። ከነዚህ ሶስት መቶ ሀያ አራት ሺህ (324,000) የሚሆኑት ከትግራይ ሲሆኑ ሰላሳ ሺህ

(30,000) የሚሆኑት ደግሞ ከዓፋር የኤርትራ አዋሳኝ አከባቢዎች የተፈናቀሉ መሆናቸው ምንጩ ይጠቅሳል።

እነዚህ ከትግራይ የኤርትራ አዋሳኝ አከባቢዎች የተፈናቀሉት ዜጎች ከጦርነቱ በኃላ በነበሩት ሁለት ተከታታይ አመታት ሲሰጥ የነበረው የማቋቋምያ ገንዘብ 134,675 የሚሆኑት በተመሳሳይም ከዓፋር አከባቢ ከተፈናቀሉትም 41 በመቶ የሚሆኑት ተጠቃሚ ያላደረገ እንደነበር በወቅቱ UN OCHA-EUE አሳውቆ ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት በወቅቱ የተፈናቃዮች ብዛትን አስመልክቶ ያወጣው መረጃም የሚከተለውን ይመስላል።

| ተፈናቃይ | ትግራይ | ዓፋር | ድምር |
|---|---|---|---|
| ብዛት በሰው ቁጥር | 330,000 | 33,901 | **363,901** |
| ብዛት በአባወራ ቁጥር | 82,500 | 8,475 | **90,975** |

*ምንጭ የኢ/ያ.መ*

ከዚህም በተጨማሪ በሁለቱ የጦርነት አመታት ብቻ በኤርትራ ይኖሩ የነበሩ 70,000 ዜጎችም ጦሩነቱን ተከትሎ የኤርትራ መንግስት በወሰደው እርምጃ ወደ ኢትዮጵያ በግዳጅ እንዲመለሱ አድርጓል። ከነዚህም ዩኒሴፍ እ.አ.አ. መጋቢት 2003 እንዳስታወቀው 85 በመቶ የሚሆኑት ወደ ትግራይ ክልል የተመለሱ ናቸው። እነዚህ በጦሩነቱ ምክንያት የተባረሩት ዜጎች ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ የተወሰኑት ዘመድ አዝማድ በማፈላለግ ከህብረተሰቡ ጋር በመቀላቀል ህዝቡ ካለው የድህነት ኑሮ በመካፈል ለመኖር የተገደዱ ሲሆን በየዋሻው እና ድልድዮች ስር ለመኖር የተገደዱም በርካቶች ናቸው።

*ሰንጠረዥ 1፣ አንኳር ሂደቶች*


| ሂደት | ቀን |
|---|---|
| **ለጦሩነቱ መነሻ የሆነው ግጭት የተጀመረበት ቀን** | ሚያዝያ 28 ቀን 1990 ዓ/ም |
| **የኢትዮጵያ ፓርላማ ኤርትራ ወረራ መፈፀማ አስታወቀ** | ግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ/ም |
| **የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለቃ እንድትወጣ ጠየቀ** | ግንቦት 5 ቀን 1990 ዓ/ም |
| **የኤርትራ መንግስቲ ጉዳዩ በነፃና ገለልተኛ አካል እንዲታይ ጥሪ አቀረበ** | ግንቦት 6 ቀን 1990 ዓ/ም |
| **አመሪካና ሩዋንዳ የሰላም ሀሳብ አቀረቡ** | ግንቦት 22 ቀን 1990 ዓ/ም |
| **አመሪካና ሩዋንዳ ያቀረቡት የሰላም ሀሳብ ኢትዮጵያ ተቀበለች** | ግንቦት 27-28 1990 ዓ/ም |
| **አመሪካና ሩዋንዳ ያቀረቡት የሰላም ሀሳብ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተቀባይነት አገኘ** | ሰኔ 1-3 1990 ዓ/ም |
| **ከሰላም ሀሳቡ በመነሳት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ባለ 11 ነጥብ የሰላም ሀሳብ አቀረበ** | ሰኔ 11 ቀን 1990 ዓ/ም |
| **የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ባለ 11 ነጥቡን የሰላም ሀሳብን ደገፈ** | ሰኔ 19 ቀን 1990 ዓ/ም |
| **ባለ 11 ነጥቡ የሰላም ሀሳብ በኢትዮጵያ ጠቀባይነት አገኘ** | ህዳር 3 ቀን 1991 |

| | |
|---|---|
| | ዓ/ም |
| ባድመ ላይ የማጥቃት ውግያ በኢትዮጵያ ተጀመረ | ጥር 29 ቀን 1991 ዓ/ም |
| ኤርትራ የአፍሪካ አንድት ድርጅት የሰላም ሀሳብን እቀበላሎህ አለች ኢትዮጵያ በበኩልዋ አሜኔታ የለኝም በማለት ውድቅ አደረገችው | የካቲት 20 ቀን 1991 ዓ/ም |
| ኢትዮጵያ ከፍተኛ የማጥቃት ዘመቻ አካሄደች | ግንቦት 4 ቀን 1992 ዓ/ም |
| ኤርትራ ከያዘችው ቦታ ለቃ እንደምትወጣ አስታወቀች | ግንቦት 17 ቀን 1992 ዓ/ም |
| ሁለቱም ወገኖች አልጀርያ አልጀርስ ላይ ንግግር ጀመሩ | ግንቦት 22 ቀን 1992 ዓ/ም |
| ኢትዮጵያና ኤርትራ የቶክስ አቁም ስምምነት አደረጉ | ሰኔ 11 ቀን 1992 ዓ/ም |
| ኢትዮጵያና ኤርትራ የአልጀርሱ የሰላም ስምምነት ተፈራረሙ | ታህሳስ 3 ቀን 1993 ዓ/ም |
| ሄግ የተሰየመው የቦርደር ኮምሽን ብይን አስተላለፈ | ሚያዝያ 5 ቀን 1994 ዓ/ም |

## 8. የሀያ አመቱ የጦርነት ቀጠናው ሁኔታ እና ህዝቡ

በዚህ ለሃያ አመታት በዘለቀው እና ሰላም በሌለበት ሁኔታ ዋና ተጠቂ የሆኑት የዓፋርና የትግራይ ክልል ህዝቦች በተለይ የኤርትራ አዋሳኝ አከባቢዎች ሰፊ ቦታ የሚሸፍን እና ወደ ሁለት ሚልዮን (2,000,000) የሚሆን ህዝብ የሚኖርበት አከባቢ ነው።

### 8.1. በትግራይ በኩል የሚገኘው በጦርነቱ ጊዜና ከዛ በኃላ ተጠቂ የሆነው ቀጠና




በትግራይ ክልል ካሉት 36 ወረዳዎች 12 ወረዳዎች በቀጥታ ከኤርትራ ጋር የሚዋሰኑ ሲሆኑ በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ያሉ ናቸው (ከላይ በካርታው ላይ በቀይ ቀለም

የተቀባው)። እነዚህም ከማእከላዊ ዞን የኣሕፈሮም እና መረብለኸ ወረዳ፣ ከምስራቃዊ ዞን የጉሎ-መኸዳ፣ ጋንታ-አፈሹም፣ ኢሮብ እና ሳዕስዕ ፃዕዳ እምባ ወረዳዎች፣ ከሰሜን ምዕራብ ዞን የመደባይ ዛና፣ ላዕላይ አድያቦ እና ታህታይ አድያቦ ወረዳዎች እንዲሁም ከምዕራብ ዞን የወልቃይት፣ ቃፍታ ሑመራ እና ሰቲት ሑመራ ወረዳዎች በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚገኙ ወረዳዎች ናቸው።

በእነዚህ ላለፉት ሃያ አመታት ሙሉ የጦርነት ቀጠና ሆነው የቆዩት የክልሉ ወረዳዎች ውስጥ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ባለስልጣን ሀምሌ 2009 ዓ/ም ይኖራል በሚል ባስቀመጠው ትንበያ መሰረት 1,534,365 ህዝብ ይኖራል።


*ሰንጠረዥ 2 ፤ በትግራይ ክልል በቀጥታ ከኤርትራ ጋር የሚዋሰኑ ወረዳዎች እና የህዝብ ብዛት*

| **ዞን** | **ወረዳ** | **የህዝብ ብዛት** |
|---|---|---|
| ማእከል | ኣሕፈሮም | 205,321 |
| | መረብለኸ | 123,100 |
| | **ድምር** | **328,421** |
| ምዕራብ | ወልቃይት | 159,806 |
| | ቃፍታ ሑመራ | 118,895 |
| | ከተማ ሰቲት | 36,074 |
| | **ድምር** | **434,879** |
| ምስራቅ | ኢሮብ | 29,374 |

| | | |
|---|---|---|
| | ጉሎ መኸዳ | 98,857 |
| | ጋንታ-ኣፈሹም | 100,222 |
| | ሳዕስዕ ፃዕዳ እምባ (ማርዋ ሳውነ) | 164,582 |
| | **ድምር** | **393,035** |
| ሰሜናዊ ምስራቅ | መደባይ ዛና | 144,246 |
| | ላዕላይ አድያቦ | 130,474 |
| | ታህታይ አድያቦ | 103,310 |
| | **ድምር** | **378,030** |
| ጠቅላላ ድምር | | **1,534,365** |
| አጠቃላይ የክልሉ ህዝብ ብዛት | | **5,247,005** |


*ምንጭ CSA Populaion projection values of 2017 at zonal and wereda levels*

*ቻርት፤ በጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ከአጠቃላይ የክልሉ ህዝብ አንፃር*



ከላይ ያለው ቻርት እንደሚያመለክተው 23 በመቶ የሚሆነው የትግራይ ህዝብ ባለፈው 20 አመታት በሰላም እጦት እየኖረ ያለው በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ነው

## 8.2. በዓፋር በኩል የሚገኘው በጦርነቱ ጊዜና ከዛ በኃላ ተጠቂ የሆነ ቀጠና




በዓፋር ክልልም በተመሳሳይ ከኤርትራ ጋር በቀጥታ የሚዋሰነው የክልሉ ቦታ ሰፊ ነው። በክልሉ ካሉት ወረዳዎች አራቱ ማለትም በራህለ፣ ዳሉል፣ አፍዴራ እና ኤሊዳር የኤርትራ አዋሳኝ ናቸው። የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ባለስልጣን ሀምሌ 2009 ዓ/ም ባስቀመጠው ትንበያ


መሰረት 1.8 ሚልየን ከሚሆነው የክልሉ ህዝብ **342,467** የሚሆነው ህዝብ በዚሁ ለአስራ ስምንት አመት የጦርነት ቀጠና ሆኖ በቆየው የክልሉ ክፋይ ውሰጥ የሚኖር ነው።

*ሰንጠረዥ 3 በዓፋር ክልል በቀጥታ ከኤርትራ ጋር የሚዋሰኑ ወረዳዎች እና የህዝብ ብዛት*

| ወረዳ | የህዝብ ብዛት |
|---|---|
| **በራህለ** | 98,345 |
| **ዳሉል** | 101,524 |
| **አፍዴራ** | 40,960 |
| **ኤሊዳር** | 101638 |
| **ድምር** | **342,467** |

ምንጭ CSA Populaion projection values of 2017 at zonal and wereda levels

*ቻርት፤ በጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖረው የዓፋር ህዝብ ከአጠቃላይ የክልሉ ህዝብ አንፃር*



ከላይ በቻርቱ ላይ ማየት እንደሚቻለው በዓፋር ክልል ከሚኖረው አጠቃላይ ህዝብ 16 በመቶ የሚሆነው የሚኖረው በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ነው።

## 9. ህዝቡ እና የሁለቱ ሀገሮች የሰራዊት አሰፋፈር

አንድ ሺህ ሳላሳ ሶስት ኪ/ሜ (ከሱዳን እስከ ጅቡቲ ወሰን) በሚደርሰው የሁለቱ ሃገሮች ድንበር የኤርትራ ሰራዊት በሁሉም ቦታዎች ማለት በሚያስችል መልኩ ህዝቡን ወደኃላ በማድርግ ነው የመሸገው። በተፃራሪው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት በሚበዛው የድንበሩ አከባቢዎች መሽጎ የሚገኘው ብዙ ቁጥር ያለው ህዝብ ከፊት እና ከጎን በመተው ነው፡፡ ይህ ማለት በነዚህ የኤርትራ አዋሳኝ በሆኑት የገጠር ቀበሌዎች የሚኖረው ህዝብ የሁለቱ ተቀናቃኝ ሀገር ወታደሮች መሃል አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ነው ማለት ነው፡፡ የጥናት ቡድኑ በበርካታ አካባቢዎች ማየት እንደቻለው እና የአከባቢው ነዋሪዎችም እንደሚያረጋግጡት በርካታ ህዝብ የሚኖሩባቸው ቀበሌዎችና ህዝቡ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት እና የኤርትራ የመከላከያ ሰራዊት ምሽጎች መሀል ላይ ሆኖ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለብዙ አመታት የሂወት፣ ንብረት እና ስነልቦና ጉዳት የደረሰበት ነው፡፡

ለምሳሌ በትግራይ ክልል ማእከላዊ ዞን ውስጥ ካሉት የኤርትራ አዋሳኝ ከሆኑት የመረብለኸ እና የአሕፈሮም ወረዳዎች ውስጥ ካሉት ቀበሌዎች አሕፎሮም የሚገኙት 6ቱ የገጠር ቀበሌዎች እና መረብለኸ የሚገኙት 8ቱ ቀበሌዎችን ጨምሮ 14ቱ ቀበሌዎች በኤርትራና በኢትዮጵያ ኃይሎች ምሽግ መሀል ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በዚህም የኤርትራ ወታደሮች ብዙ ጊዜ ዜጋቸዉ ኮብልሎ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ወይም ወታደሮቻቸው ሲኮበልሉ በተደጋጋሚ ቶኮስ ስለሚከፍቱ ለእነዚህ የተተኮሰ ጥይት ቀድሞ የሚያገኘው እና የሚያርፈው ከፊት በሰፈረው ህዝብ እና ንብረት ላይ መሆኑንና በዚህም ምክንያት ብዙ ጉዳት የደረሰ መሆኑን ህብረተሰቡ በአንደበቱና በምሬት የሚገልፀው ነው፡፡

በየጊዜው በኤርትራ ሰራዊትም ሆነ በኢትዮጵያ ሰራዊት ተነሳሽነት በሚወስዷቸው የማጥቃትና የትንኮሳ ግጭቶች ባካባቢው ያሉ ህዝቦች የግጭቱ ሰለባ በመሆን ብዙ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ለዚሁ ጥሩ ማሳያ በፆሮና ግንባር በኢሮብ አከባቢ የተደረጉ ግጭቶች በኗሪው ህዝብ ብዙ ጠባሳና ኪሳራ አስከትሏል። በሌሎች አከባቢዎችም በተመሳሳይና ከዚህ በተጨማሪም በሁለቱም በኩል ሲሰራበት የነበረው የተለያዩ ታጣቂ ተቃዋሚ ሀይሎች የሚያካሂዱትን የውክልና ጦርነት (ግጭት) ሰለባ በመሆን ህዝቡ ማቋራጫ በሌለው መልኩ ጉዳት ደርሶቦታል። በዚህም ህዝቡ የበርካታ ሂወት፣ ንብረት እና የስነልቦና ጉዳት ሰለባ ሆኗል።

በጠረፍ አከባቢ ያለው ከሁለት ሚልዮን የማያንሰው የትግራይና የዓፋር ህዝብ በሁለቱም ሀገራት ማለትም በኢትዮጵያና በኤርትራ መደበኛ ሰራዊት ፍጥጫና ሁለቱም ሀገሮች በተከተሉት የውክልና ጦርነት (ግጭቶች) ህዝቡ በዚህ ሁኔታ መሀከል ተቀርቅሮ፣ የችግሩ ሰለባ ሆኖ፣ በመንግስትና በክልሎቹ መስተዳድሮችም ለተሸከመው ዘርፈ ብዙ ችግር ግምት ተነፍጎት የችግሩ ሰለባ ሆኖ፣ ብዙ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የሞራል፣ የሂወት እና ስነ-ልቦና ውድ ዋጋ ከፍሎ፣ አሁን ባለበት ሁኔታ ሲታይ በርሷል ማለት ይቻላል።

በነዚህ በኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት እና በኤርትራ የመከላከያ ሰራዊት ምሽጎች መሀል ውስጥ ለጥቃት ተጋልጠ ላለፉት 18 አመታት ሙሉ እየኖረ ያለው ህዝብ ብዛትም እጅግ በርካታ ነው፡፡

በክሉሉ ማእከላዊ ዞን በመረብ-ለኸ እና አሕፈሮም ወረዳዎች ብቻ 328,421 የሚሆን ህዝብ በእንደዚህ አይነት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ለመኖር ተገዷል፡፡

*ሰንጠረዥ 4 በቶክስ ቀጠና ውስጥ የሚኖር ህዝብ ትግራይ ማእከላዊ ዞን*

| **ወረዳ** | **በኢትዮጵያ እና በኤርትራ ኃይሎች መሀልና በቶክስ ቀጠና ውስጥ የሚኖር ህዝብ በዛት** |
|---|---|
| **ኣሕፈሮም** | 205,321 |
| **መረብለኸ** | 123,100 |
| **ድምር** | **328,421** |

*ምንጭ* CIC *ለ*2007 *ዓ/ም ያስቀመጠው የህዝብ ብዛት ትንበያ*

ከነዚህ ሁለት ወረዳዎች በቀበሌ ደረጃ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለማሳየትም ለምሳሌ፡- መረብ-ለኸ ወረዳ ውስጥ አዲ ሹምብሩክ ማይወዲ-ዓምበራይ እና ጠራውር የሚባሉት ቀበሌዋችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በነዚህ ቀበሌዎች ምንም የመከላከያ ኃይል የሌላቸው እንደሚገኙም ለማወቅ ችለናል፡፡ ከእነዚህ ለምሳሌ፡ ዓዲ-ጋባት፣ ደብረ-ሓርማዝ፣ ሀፍተ-ማርያም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖረው የህዝብ ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ማየት ይቻላል፡፡

*ሰንጠረዥ 5 መረብ-ለኸ ወረዳ በቶክስ ቀጠና ውስጥ የሚኖር ህዝብ*

| **ተ.ቁ** | **ቀበሌ** | **የህዝብ ብዛት** |
|---|---|---|
| 1. | **ማይ-ወዲ-ዓሞበራይ** | 4,000 |
| 2. | **ዓዲ-ሹም-ብሩክ** | 3,000 |
| 3. | **ጠራውር** | 3,500 |
| 4. | **ዓዲ-ገባት** | 5,000 |
| 5. | **ደብረ-ሐርማዝ** | 4,000 |
| 6. | **ሃፍተ-ማርያም** | 2,500 |
| | **ድምር** | **16,500** |

*ምንጭ የትግራይ ክልል ማእከላዊ ዞን የፀጥታ ፅ/ቤት*

እነዚህ ምንም የመከላከያ ኃይል የሌለባቸውና በወረዳው ውስጥ የሚገኙት ምልሻ የሚጠብቃቸው ቀበሌዎች ሰፊ ቦታ የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ዓዲ-ፍታው ከሚባለው አንድ የወረዳው ጫፍ ወደ ምዕራብ በኩል ወደ ምትገኘው ተባይ ቀበሌ የአራት ሰዓት ተኩል የእግር ጉዞ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ከጠራውር እስከ ማይ-ወዲ-ዓምበራይ ያለው እና በምልሻ የሚጠበቀው አካባቢ የ5 ሰዓት የእግር ጉዞ ይሆናል፡፡

በትግራይ ክልል የምስራቃዊ ዞን አከባቢ ያለው ሁኔታም ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚህ ዞን በጦርነት ቀጠናው የሚገኙት ወረዳዎች ኢሮብ፣ ጉሎ-መኽዳ እና ጋንታ-አፈሹም ናቸው፡፡ ከጉሎ-መኽዳ ወረዳ የሚበዙት ቀበሌዎች እና ህዝቡ ወደ ኤርትራ ጦር ምሽግ ተጠግቶ የሚኖር ነው፡፡ ይህንን በምሳሌ ለመጥቀስ ኪሊንቶ ከሚበለው የወረዳው ቀበሌ ሰቦያ እስከሚበለው ቀበሌ ድረስ ያለው ህዝብ ማየት ይቻላል፡፡

በኢሮብ ወረዳም እንደ ወረዳ በሙሉ በእንደዚህ አይነት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ነው፡፡ ለምሳሌ በኢሮብ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙት ዓውጋ፣ ዩንጋ እና ዒንዳሌ ከሚባሉት አከባቢዎች ጫፍ ጀምሮ እስከ ጉንዳጉንዶና አራዕ (ልዩ ስሙ ደምሓለ) እስከሚባለው አከባቢ ድረስ ያለው ህዝብ በኤርትራ ጦር ምሽግ ስር እና በቶክስ ርቀት የሚኖር ህዝብ ነው፡፡ በነዚህ በተጠቀሱት አከባቢዎች በተለይ ዳልጌዳ፣ ወርዓትለ፣ አገርሎኮማ እና ኣራዕ የሚባሉት ቀበሌዎች ነዋሪ ህዝብ ሙሉ በሙሉ በኤርትራ ምሽግ ጥግ በመሆን ሲማቅቅ የኖረና ያለ ህዝብ ነው፡፡ ይባስ ብሎም ችግሩን የሚናገርለትና የሚሞግትለት ያጣም ህዝብ ነው።

ሌላው የክልሉ ምስራቃዊ ዞን የሚገኘው የጉሎመኽዳ ወረዳ ህዝብ እና የሰራዊቱ አሰፋፈር ያየን እንደሆነም ተመሳሳይ ነው፡፡ የድንበር ግጭቱ ቀዳሚ ሰለባ ከሆኑት አከባቢዎች አንድዋ የሆነችው ዛላአምበሳን (ንኡስ ወረዳ) ጨምሮ ሰቦያ፣ ማርታ፣ አዲስ-ተስፋ እና ዳሞ

አከባቢ ያለው መዛብር ቀበሌ ነዋሪ ህዝብ ሙሉ በሙሉ ወደ የኤርትራ ምሽግ ተጠግቶ ለመኖር የተገደደ ህዝብ ነው፡፡ በዞኑ የጋንታ አፈሹም ወረዳ ውስጥ የሚገኘውና ከመዛብር ጋር አዋሳኝ የሆነው የውህደት ቀበሌ ህዝብ አሰፋፈርም በተመሳሳይ ሁኔታ የተጎዳ ህዝብ ነው፡፡

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት እና ሌሎች በጦርነት ቀጠናው ውስጥ ያሉት አከባቢዎች ያለው ህዝብ በኤርትራ ምሽግ በቅርብ ርቀት እየኖረ ነው ብቻም ሳይሆን በአንዳንድ አከባቢዎች ህዝቡ የሚኖርባቸው መንደሮች ከኤርትራ ጦር ምሽግ ያላቸው ርቀት ከ50 ሜትር አይበልጥም፡፡ ይህም የሚያሳየው በኤርትራ ሰራዊት ይሁንታ ውስጥ ሆኖ በሞትና በሂወት መሀከል ሲማቅቅ የኖረ ህዝብ መሆኑ ነው። ለአደጋ ከመጋለጥ ውጭ ሌላ አማራጭ ያላገኘና ከለላ ያላገኘ ህብረተሰብ ነው።

ለምሳሌ ኢሮብ ወረዳ የሚገኘው ማይጫዓ ቀበሌ የወሰድን እንደሆነ የቀበሌው ህዝብ የሰፈረበት ቦታ ከኤርትራ ጦር ምሽግ ያለው ርቀቱ በጣም አጭር እና በጠላት ቶክስ ርቀት ውስጥ ነው፡፡ በሁለቱም ሀገሮች ሀይሎች ምሽግ ማሃል ላይ ያሉና የኤርትራ ምሽግ አፍንጫ ስር የሚገኙት አዲስ-ተስፋ፣ ጉልትና-ዓድና፣ ኪኒንቅሊንቶ፣ አያሓና መኪታ የተባሉት አከባቢዎች ያለው ርቀትም ተመሳሳይ ነው ፡፡ የዛላአምበሳ ከተማ ከኤርትራ ምሽግ ያላት ርቀት ያየን እንደሆነም በጠላት የተከበበች ከመሆንዋ በተጨማሪ እንደ ከተማ በኤርትራ ጦር የቶክስ ርቀት ሆና ህዝቡ የሰው ኑሮ እየኖረ ነው ለማለት የማይቻል ነው፡፡

በአጠቃላይ በብዙ የድንበሩ አከባቢ የሚገኘው የኢትዮጵያ የመከላከያ ሀይል አሰፋፈር ሲታይ ህዝቡን ከፊት በማድረግ እና ሙሉ በሙሉ ከታጠቀው መደበኛ የኤርትራ ጦር ጋር በማጋፈጥ ለስትራቴጂ ያመቸኛል ባለው ባብዛኛው ጉቡታ ቦታዎች ላይ ነው ሰፍሮ የሚገኘው፡፡ በብዙ ቦታዎች የህዝቡን (መንደሮች፣ ቀበሌዎች) ኗሪ የሆነውን ህዝብ

ደህንነትና ቅኝት የሌለው ስለሆነ ብዙ ህዝብ ለአደጋ የተጋለጠበት፣ ይባስ ብሎም የህዝቡን ደህንነት በብዙ አከባቢ ለአከባቢው ምልሻ እንዲሆን በማድረግ ህዝቡ ከባድ ችግር ውስጥ እንዲወድቅ ያደረገና ብዙ ዋጋ ህዝቡ እንዲከፍል ያስገደደ ነው። በሌላ በኩል በመግብያው ላይ እንደተገለፀው በአብዛኛው የኤርትራ ጦር አሰፋፈር ሲታይ ግን ከኪኒን ቅሊንቶ ከፊል አከባቢ በስተቀር ህዝብ ከፊት በመተው የመሸገበት ቦታ የለም ማለት ይቻላል፡፡

## 10. የምልሻ ተሳትፎና ተግዳሮቶቹ

የዚህ አከባቢ ህዝብ ላለፉት 18 አመታት የተሸከማቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖምያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ስነልቦናዊ ችግሮች ሰፊ እና በርካታ ናቸው። በተለይ በዚህ አከባቢ ያሉት የምልሻ ሀይሎች ላይ ያለው ጫና እና የሰቆቃ ኑሮ ደግሞ እጅግ የከፋ ነው።

የክልሉ ምልሻ ህጋዊ አደረጃጀት እና ሀላፊነትን በሚመለከት ስራ ላይ ያለው አዋጅ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሽያ ጽህፈት ቤት እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 194/2003 ነው። በዚህ አዋጅ መሰረት "ምልሻ" ማለት በህዝብ ተመልምሎ የአከባቢው ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር በመንግስት እውቅና የተሰጠው ታጣቂ ሀይል መሆኑን ይገልፃል፡፡ በአዋጁ ቁጥር 10 ላይ እንደተደነገገውም፤

> *በዚህ ሁኔታ የተደራጀው የምልሻ ሀይል ለብዙ ግዜ ከኑሮውና ከምርት ስራ የሚነጥል የፀጥታና የሌሎች መንግስታዊ ስራዎች ሊሰጠው ኣይገባም፡፡ ለመፈፀምም አይገደድም።*

በሚል በግልፅ የተቀመጠ ቢሆንም በተግባር ላይ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ያየን እንደሆነ ግን አዋጁን የሚፃረር እና ምንም አይነት ህጋዊ መሰረት የሌለው ነው።

ለምሳሌ በትግራይ ክልል በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ባሉት ወረዳዎች ብቻ በበርካታ አስር ሺዎች የሚቆጠሩ የምልሻ አባላት ይገኛሉ። እነዚህ ታጣቂዎች መደበኛ እና ፀረ

ሽፍታ ምልሻ የሚል ሁለት አይነት ስያሜ ይዘው የተደራጁ ናቸው። ከነዚህም በተለይ ፀረ ሽፍታ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው የምልሻ አባላት፣ የምልሻ ማቋቆምያ አዋጁን ወይም ሌላን ህግ መሰረት ያላደረገ ስያሜ፣ አደረጃጀት እና ተልእኮ የተሰጣቸው ናቸው። እነዚህ በማንኛውም የህግ ማእቀፍ ያልተደራጁ ነገር ግን በከፊል በምልሻ አዋጁ የሚተዳደሩ ታጣቂዎች ላለፉት 18 አመታት በምሽግ፣ ቋሚ የመደበኛ ሰራዊትና ማቋረጫ በሌለው የተንቀሳቃሽ የፀጥታ ግዳጅ ያለምንም ክፍያ፣ ጥቅማጥቅም እና ምንም አይነት እውቅና ሳይሰጣቸው የመደበኛ የመከላከያ ሰራዊት ስራን ሸፍነው የሀገራቸውን ድንበር ሲጠብቁ ነው የኖሩት።

*ሰንጠረዥ 6፣ በትግራይ የኤርትራ አዋሳኝ ወረዳዎች ላይ የተሰማራው የምልሻ ብዛት*

| **ዞን** | **ወረዳ** | **የምልሻ ብዛት** | **የፀረ ሽፍታ ብዛት** | **የሁለቱም ድምር** |
|---|---|---|---|---|
| **ማእከል** | ኣሕፈሮም | | 450 | **10936** |
| | መረብለኸ | | 486 | |
| | **ድምር** | **10000** | **936** | |
| **ምዕራብ** | ወልቃይት | | | **11018** |
| | ቃፍታ ሑመራ | | | |
| | ከተማ ሰቲት | | | |
| | **ድምር** | **10938**<br><br>**523 ተጠባባቂ** | **80** | |
| **ምስራቅ** | ኢሮብ | 876 | 58 | **4341** |
| | ጉሎ መኸዳ | 1008 | 61 | |
| | ጋንታ ኣፈሹም | 1900 | 8 | |
| | ሳዕስዕ ፃዕዳ እምባ (ማርዋ ሰውነ) | 340 | 92 | |
| | **ድምር** | **4122** | **217** | |
| **ሰሜን ምዕራብ** | መደባይ ዛና | | | |
| | ላዕላይ አድያቦ | | | |
| | ታህታይ አድያቦ | | | |
| | **ድምር** | **17233** | **120** | **17353** |
| **ድምር በ4 ዞኖች** | | **42413** | **1353** | **43766** |

*ምንጭ  የክልሉ የዞንና ወረዳ እንዲሁም የፀጥታ ፅ/ቤቶች*

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ የተቀመጠው ይህ የምልሻ ሀይል በማያቋርጥ ግዳጅ ለ18 አመታት ከእርሻውና ከኑሮው እየተፈናቀለ ከአቅሙ በላይ በሆነ መልኩ፣ ህጋዊ መሰረትም ሳይኖረው በተሳሳተ አጠቃቀምና ስምሪት እንዲማስን የተደረገ ነው።

እነዚህ የምልሻ ታጣቂዎች የሚሰጣቸው ወጥነት ያለው መደበኛ ደሞዝ ወይም ሌላ ጥቅማጥቅም የለም ብቻም ሳይሆን ከኑሯቸው እና ከምርት ስራ ርቀው ምሽግ ውስጥ ገብተው የመደበኛ የመከላከያ ሰራዊት ስራ በሰሩባቸው 18 አመታት ሙሉ የሚቀርብላቸው ቀለብ፣ አልባሳት፣ ጫማ፣ የህክምና መስጫ ቁሳቁስ፣ የህክምና አግልግሎት ይሁን ሌላ ምንም አይነት አቅርቦትም ይሁን አገልግሎት የሌላቸው ሆነው፣ ያሳለፉት የሰቆቃ እና የባርነት ሂወት የከፋ ነው።

በምልሻ መተዳደርያ ደንቡ መሰረት ምልሻው ከቀበሌው ውጭ እንዲንቀሳቀስ የማይፈቀድ ቢሆንም የኤርትራ አዋሳኝ በሆኑት ወረዳዎች ላይ ያሉት እና ፀረ ሽፍታ በሚል የሚታወቁት ታጣቂዎች፣ ከመከላከያ ሰራዊቱ ጋር ምሽግ ውስጥ ገብተው ከሚያከናውኑት የመደበኛ ወታደር ስራ በተጨማሪ እስከ 6 ሰዓት የሚደርስ የእግር ጉዞ እየተጓዙ ዳሰሳ ያካሂዳሉ ይጠብቃሉ፡፡

በተለይ በትግራይ ክልል ማእከላዊ ዞን ውስጥ ባሉት ሁለቱ የኤርትራ አዋሳኝ ወረዳዎች የኤርትራ ሰላዮችና የደፈጣ አጥቂዎች በብዛት ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ምልሻው ከእነዚህ ኃይሎች ጋር እየተጋፈጠ ሰላይ እና ኮብላይ የኤትርራ ወታደሮችን እየያዘ ያስረክባል፡፡ ታድያ ለዚህ ስራ የሚሆን መጓጓዣ መኪና እንኳን የለውም፡፡ ይህንን ስራ ለማከናወን ምልሻው እስከ 4 እና 5 ሰዓት በእግር ተጉዞ ምርኮኞችንና እስረኞችን በማስረከብ በእግር ተመልሶ ምሽግ ውስጥ ገብቶ ይጠብቃል፡፡ የምልሻው ስራ የሙሉ ጊዜ ስራ ነው። አንድ ምልሻ ወደ

ስራ ሲሰማራ ስንቅ፣ ማብሰያ፣ ዱቄት ከቤቱ ይዞ ቢያንስ ከ 8 እስከ 10 ቀን ሳይመለስ በግዳጅ እንዲቆይ የሚደረግ መሆኑ ምልሻዎቹ በራሳቸው የሚገልፁት ነው።

*የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የሚልሻ አባላት መተዳደርያ ደንብ ቁጥር 70/2004 መሰረት ግን ምልሻው ወደ ተልእኮ ሲሰማራ ስንቅ፣ ቀለብና የህክምና አገልግሎት ካሰመራው አካል ያገኛል በሚል ተደንግጓል።*

እነዚህ የክልሉ የምልሻ ታጣቂዎች በኤርትራ ወታደሮችና በታጠቁ ተቃዋሚዎች ከሚደርስባቸው ጥቃት ባሻገር በእባብና ሌሎች መርዛማ ተህዋስያን የሚገጥማቸው ችግርም በብዛት እንደሆነና መፍትሄም ያጡለት ችግር እንደሆነ ምልሻዎቹ በምሬት የሚገልፁት ነው። ምልሻው በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲጠቃ ወይም ሲታመም የህክምና አገልግሎት ወይም ካሣ ማግኘት የሚችለው በሀኪም ማረጋገጥ ሲችል በመሆኑ እና ለማረጋገጥም ቀላል ስለማይሆን ጥቃት ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰው ሊያገኝ የሚገባው የህክምና አገልግሎት ወይም ካሣ ማግኘት አይችልም፡፡ ወይም ከባድና ብዙ የቢሮክራሲ ውጣ ውረድ እንዳለው ምልሻዎቹ ያረጋገጡት ጉዳይ ነው።

*ይሄም አንድ ምልሻ ተልእኮውን በመፈፀም ላይ እያለ ለደረሰበት ጉዳት ወይም ህመም አስፈላጊውን የህክምና ወጪ ባሰማራው አካል የሚሸፈን ይሆናል፣ በሚል የተደነገገውን የሚፃረርና በትግበራ ላይ ከፍተኛ ችግር ያለበት መሆኑን ነው እንደ ምልሻዎቹ አገላለፅ።*

ሌላው በማቋቋምያ አዋጁ ላይ የምልሻው መብትን የስምሪት ስራን እና የህግ ከለላን አስመልክቶ የሚከተለውን ይላል።

*ከስምሪት ስራ ጋር በተያያዘ በፈፀመው ተግባር ምክንያት በሶስተኛ ወገን ለሚቀርብበት ክስ ባሰማራው አካል ወጪ የጥብቅና አገልግሎት ያገኛል።*

ይህ በደንቡ ላይ የተጠቀሰ መብት ቢሆንም በተግባር ላይ ያለው እውነታ ግን ከዚህ በእጅጉ የሚርቅ ነው። ሌላ ቀርቶ ምልሻው ሽፍታን እና ሰላይን እያጠቃ ባለበት ሁኔታ እንኳን ተኩሶ ሲገድል የህግ ከለላ የሚያገኝበት አሰራር የለም፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሽፍታ ከአንድ የምልሻ አባል መሣሪያ ቀምቶ በቦታው ላይ በነበሩ 6 የምልሻ አባላት ላይ እየተኮሰ ወደ ኤርትራ ሲያመልጥ የነበረን ሽፍታ ተኩሰው በመግደላቸው ምክንያት ሰው ገድላችኋል በሚል ተጠያቂ የሆኑና የተከሰሱ የትግራይ ማእከላዊ ዞን የምልሻ አባላት እንዳሉ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከተለያዩ የምልሻ አባላት እና አመራሮች ያገኘነው መረጃ እንደሚያሳየው አንድ ምልሻ ተረኛ ሆኖ ባልተመደበበት ቀን ሾልከው ከሚገቡ የኤርትራ ሰላዮች ጋር እየተዋጋ ሲቆስል ወይም ሲሞት በእለቱ ተረኛ ጠባቂ ነህ ተብሎ ባለመመደቡ ምክንያት ካሣ አይከፈለውም፡፡ ይህ በተጨባጭ ወልቃይት ወረዳ ላይ ያገጠመ ሀቅ እንደሆነ ምልሻዎቹ ይናገራሉ፡፡



*ትግራይ ከሚገኙ የተወሰኑ የምልሻ አባላት ጋር የተደረገ ውይይት (ገርሁ-ስርናይ)*

በክልሉ ሰሜን ምዕራብ ዞን ወስጥ ካሉት የኤርትራ አዋሳኝ ወረዳዎች ማለትም መደባይ-ዛና፣ ላዕላይ-አዲያቦ እና ታሕታይ-አዲያቦ ላይ ደግሞ ከሌላው ለየት በሚል መልኩ ባካባቢው ያሉት ፀረ ሽፍታ በሚል የተደራጁት ኃይሎች ብቻ ሳይሆኑ ምልሻ በሚል የተደራጁት ታጣቂዎችም ጭምር ናቸው የመደበኛ ወታደር ስራ እየሰሩ የሚገኙት፡፡ በዚሁ ዞን ውስጥ የሚገኘው የቃፍታ ሑመራ ብሄራዊ ፓርክን የመጠበቅ ስራም ለምልሻው የተተወ ነው፡፡ የክልሉ የምዕራብ ዞን ደግሞ የሚዋሰነው ከኤርትራ ብቻ ሳይሆን ከሱዳንም ጋር ነው፡፡ ስለዚህ በሱዳን በኩል ሊገቡ የሚችሉ አሸባሪዎችን የመጠበቅ እና የኮንትሮባንድ ንግድ የመቆጣጠር ስራም በዋናነት የሚከናወነው በዞኑ የምልሻ አባላት ነው፡፡ ይህንን ከባድ ግዳጅ ሲፈፅሙ ግን እዚህ ላይም ነፃ ግልጋሎት እንጂ ምንም አይነት ድጋፍና አቅርቦት የላቸውም።

ሌላው እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ጉዳይ በተሻሻለው የክልሉ የሚልሻ ኣባላት መተዳደርያ ደንብ ቁጥር 70/2004 ላይ በተጠቀሰው መሰረት የምልሻ አባል መሆን ያለባቸው እድሜው ከ18 እስከ 45 ዓመት የሆነ ነው በሚል ቢደነገግም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው በእድሜ የገፉ ምልሻዎች እንዳሉ ምልሻዎቹ ይገልፃሉ።

እነዚህ ከኑሯቸው እና ከስራዎቻቸው ርቀው በድህነት እና ችግር ውስጥ ሆነው የሀገሪቱን ተልእኮ የሚፈፅሙት ታጣቂዎች ታድያ በአንድ በኩል በመተዳደርያ ደንቡ ላይ የተቀመጠላቸውን መብቶችንም ጭምር የተነፈጉ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ደንቡ ላይ የተጠቀሱት አስገዳጅ ሁኔታዎች እና ቅጣቶች ግን ተግባራዊ ስለሚደረጉባቸው የቅጣቱ ሰለባ ናቸው። በደንቡ መሰረት እያንዳንዱ የምልሻ አባል ላጠፋው ወይም ላባከነው ንብረት ወይም ትጥቅ እስከ ብር 18,000 (አስራ ስምንት ሺ ብር) እንዲከፍል ይገደዳል። ይባስ ብሎም ለመብታቸው ምንም ግምት ሳይሰጣቸው በጣም ከባድና ጥብቅ የአፈፃፀም መመርያ

ስር የወደቁ ናቸው። ሙሉ ይዞቱን መረዳት የሚፈልግ የአተገባበር መመርያው ከክልሉ የፀጥታ ዘርፍ ወስዶ በማንበብ መረዳት ይቻላል። የቃፍታ ሑመራ ብሄራዊ ፓርክ ልክ እንደሌሎች ፓርኮች መንግስት በሚመድበው በጀትና የጥበቃ ሀይል ከማስጠበቅ ይልቅ ክልሉ በነፃ ጉልበት በምልሻው እንዲጠበቅ ለምን እንደተደረገ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡

## 11. የአካባቢው ኗሪ ህዝብ አስከፊ ኑሮ

የጥናት ቡድኑ በዚህ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ያለውን ሁኔታ ለመቃኘት ሲንቀሳቀስ በቅድምያ ያቀናው ወደ ዛላአምበሳ ከተማ ነው፡፡

በታታሪነቱ የሚታወቅ ህዝብ የሚኖርባት ዛላአምበሳ ከተማ ከጦርነቱ በፊት ደህና የሚባል የንግድ እንቅስቃሴ የነበረበት አካባቢ ነው፡፡ ባለፉት 20 አመታት ግን ሁኔታው ኩፉኛ ተቀይሯል ንግድም ይሁን ሌላ ማንኛውም ማህበራዊ ሂወትና እንቅስቃሴ ኩፍኛ ተጎድቷል፡፡ የከተማው ህዝብ ከመንግስት ሰራተኛው በስተቀር ጎስቃላ ኑሮውን እየመራ የሚገኘው በሚለገስለት ለ20 ዓመት የዘለቀ የስንዴ ምፅዋት ነው፡፡

ሁሉም የዛላአምበሳ ህዝብ ጦርነቱ ሲጀመር ቀየውን ጥሎ ወጥቶ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ህዝቡ ሲወጣ አንድ ቅያሪ ልብስ እንኳን ሳይዝ ነው ባዶ እጁ ወደ አዲግራት ተፈናቅሎ የወጣው፡፡

የሰላም አስከባሪው በስፍራው ሲሰማራ ነዋሪው ወደ ፈራረሰችው ከተማው እንዲመለስ የተደረገ ሲሆን የሰላም አስከባሪው ከስፍራው ከወጣ በኋላ ደግሞ ችግሩ የተባባሰበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ የሰላም አስከባሪው በቦታው በነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ነዋሪው ወደ ከተማ የተመለሰ ቢሆንም በዛን ወቅት የተኩስ ልውውጥ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ከዚያ በኋላ እና የኤርትራ ሰራዊት ምሽግ ወደ ከተማው ከተጠጋ በኋላ በየጊዜው የሚነሳ የቶኩስ ልውውጥ ስላለ ሁሌም አካባቢው በስጋት የሚኖር ከመሆኑም በላይ በሚቶኮስ ጥይት የከተማዋ ነዋሪዎች ላይ በተደጋጋሚ የሂወትና የንብረት አደጋ መድረሱ ነዋሪዎች ይገልፃሉ፡፡ የዛላአንበሳ ህዝብ በኤርትራ ሰራዊት

ምሽግ ተከቦ ጠባብ መግቢያ ያለው የከብት በረት ውስጥ ገብቶ የተዘጋ ህዝብ ነው የሆነው፡፡ ወደ ከተማው ከሚያስገባው ጠባብ መንገድ በስተቀር ከተማዋ ግራና ቀኙ ከኗላም በኤርትራ ወታደሮች ምሽግ የተከበበች መንደር ሆና ከአስር ሺ የማያንስ ህዝብ እየተሰቃዬባት የነበረችና ያለች የወደመች ከተማ ነች፡፡

በዚህ ምክንያትም ህዝቡ ዘወትር በችግር፣ በፍርሀትና በጭንቀት የሚኖር ቢሆንም ሀገሬ ነው በሚል እና መሄጃ ስለሌለው ቀየውን አልለቀቀም፣ በከባድ ሁኔታ ውስጥ ከባድ ዋጋ እየከፈለ መኖርን መርጧል፡፡

የመንግስት ትኩረት አጥተናል የሚሉት የአከባቢው ነዋሪዎች መጀመሪያ አካባቢ የዞኑ አስተዳዳሪዎች በተወሰነ መልኩ በስፍራው እየተገኙ ህዝቡን ይጠይቁና ያረጋጉ እንደነበር፣ ቢገልፅም ላለፉት 18 አመታት ግን የፌደራል መንግስት ከፍተኛ አመራሮች አንድም ቀን በቦታው ተገኝተው አያውቁም በሚል በአፅንኦ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህም በላይ ህዝቡንም ሰብስበው አናግረው አያውቁም፡፡ የክልሉ መንግስት አመራሮችም ቢሆን ባለፉት 18 አመታት በአከባቢው የተገኙት ከሁለት እና ከሶስት ጊዜ እንደማይዘል ነው ነዋሪዎች የሚገልፁት፡፡

ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት የወረዳው ማእከል ዛላንበሳ ነበር፡፡ ከጦርነቱ በኋላ ህዝቡ ወደ ከተማው ሲመለስ የወረዳው አስተዳደርና የወረዳው ጽ/ቤት ግን ከህዝቡ ጋር አልተመለሱም፡፡ የፀጥታ ስጋት አለ በሚል ወረዳው ፋፂ እንዲሆን በማድረግ ዛላአንበሳ ከተማና በዙሩያዋ ያሉ ሁለት ቀበሌዎች አንድ ላይ በማድረግ ንኡስ ወረዳ እንድትሆን ነው የተደረገው ይላሉ የከተማው ነዋሪዎች፡፡ ለምን እንደዚህ ሆነ ተብለው ሲጠየቁ ታድያ፣ እንደኛ ለምን በቶክስ ስርና አደገኛ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ይቀመጣሉ ይላሉ ነዋሪዎቹ፡፡

ነዋሪው በእርዳታ መልክ የሚሰጠው የስንዴ ምፅዋት በመጠኑ ትንሽ ከመሆኑም በላይ ወቅቱን ጠብቆም አይገኝም፡፡ አንዳንዴ በሁለት ወር እና በሶስት ወር የሚደርስበት ጊዜ እንዳለ ነዋሪዎች ይገልፃሉ፡፡ እንደዚህ ዘግይቶ የሚደርሰው የእህል እርዳታ ለአንድ ሰው በ15 ኪ/ግ ስም የሚሰጥ

ቢሆንም በትክክል ሲለካ ግን ከ13 ኪ/ግ በልጦ አያውቅም ነው የሚለው የአከባቢው ነዋሪ። እያንዳንዱ ግን 15 ኪ/ግ ወስጃለሁ ብሎ እንዲፈርም ይደረጋልም ይላሉ።

በጦርነቱ ምክንያት ሙሉ በሙሉ የወደመችው የዛላንበሳ ከተማ ነዋሪዎች ለፈራረሰው ቤታቸው ሊቋቋሙበት ከብር 39,500 እስከ ብር 50,700 እንዲሰጣቸው የተደረገ ቢሆንም ነዋሪዎቹ እንደሚገልፁት ግን ገንዘቡ መልሶ ለመቋቋም በፍፁም የማይበቃ ነበር ይላሉ። የጥናት ቡድኑ በአካል ተገኝቶ ለማየት የቻለው የሚያረጋግጠውም ይህንን ነው። በከተማው መሀል ላይ የሚገኙ ቤቶችም ሳይቀር ፊት ለፊት የሚታየው ብቻ ውሱን ጥገና የተደረገለት ቢሆንም ከተማው እንደ ከተማ ሲታይ እንደወደመ ነው።

በወቅቱ የተሰጠው የመቋቋሚያ ገንዘብ ለጊዜው እንደሆነና በቂ እንዳልሆነ በቀጣይ ግን መልሶ ለመቋቋም የሚያስችል ገንዘብ እንደሚሰጥ ተነግሮን ነበር ይሉና ያም ቢሆን የውሀ ሽታ ሆኖ ነው የቀረው ይላሉ ነዋሪዎች።

በአካባቢው የነበሩ የልማት ተቋማት ለምሳሌ የወረዳ ፍ/ቤት፣ ማርታ በሚል ሲታወቅ የነበረው የከተማው አዳራሽ፣ በከተማው የነበረው አንድ የዱቄት ፋብሪካን ጨምሮ ሌሎች የመንግስት ቢሮዎች በሙሉ በወረራው ጊዜ ከወደሙ በኋላ ተመልሰው አልተገነቡም። ፈራርሰው ነው የቀሩት።



*የዛላአንበሳ ከተማ ከፊል ገፅታ*

ድሮ የዛላንበሳ ከተማ ሲባል የነበረው አሁን ስም ብቻ ነው ይዞ የቀረው ይላሉ ነዋሪዎቹ። እንደ ሌላ የህብረተሰብ ክፍል ሁሉ የከተማው ወጣቶች ችግር ደግሞ የከፋ ነው። ለወጣቶች የሚሆን የስራ እድል ምንም ነገር የለም። እንደ ነዋሪዎቹ አባባል ወጣቱ ያለው አማራጭ ስደት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ሰርቶ ለመኖር የሚያስችለው አማራጭ በጭራሽ የለም። የፋይናንስ ተቋማት የሚሰጡት የብድር አገልግሎት እንኳን መጠቀም አይችሉም። የብድር ተቋማቱ የሚጠይቁት የወለድ መጠን ሰላምና የተሻለ የስራ እንቅስቃሴ ባለባቸው አካባቢዎች ካለው የወለድ መጠን ጋር እኩል ነው። በዚህ ምክንያት ብድር መውሰድ የማያዋጣ እና ለከፍተኛ ኪሳራ ስለሚያጋልጥ መጠቀም አልቻልንም ይላሉ።

ነዋሪዎቹ ብድር አንወስድም፣ ምን ሰርተን ልንከፍለው፣ ለኪሳራ እንዳረጋለን ይላሉ። እንሞክረው  ብለው ብድር የወሰዱት የሚበዙት ለኪሣራ ስለተዳረጉ እና መመለስ ስላልቻሉ ተከሰው ፍ/ቤት ሲመላለሱ ነው የሚውሉት። አንዳንድ ወጣቶች ብድር ወስደው መመለስ ሲያቅታቸዉ ሰግተው ወደ ኤርትራ ሄደው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ታጣቂ ሀይሎች መጠቀሚያ የሆኑ አሉ። በባህር ወደ አረብ ሀገሮች የሚሻገሩና ለመሻገር ሲሞክሩ ቀልጠው የሚቀሩ ወጣቶችም በርካታ ናቸው። ለምሳሌ ከዛላምበሳ በቅርብ ርቀት በሚገኘው ኢሮብ የሚባል ወረዳ መሰረት በማድረግ አንድ በመቀሌ ዩንቨርሲቲ የተደረገ የድህረ ምረቃ ማሟያ ጥናት እንደሚያሳየው በወረዳው ከያንዳንዱ ቤት ብያንስ አንድ የቤተሰብ አባል ለስደት ተዳርጓል። (ብስራት ወ/ስላሴ 2014)

በአከባቢው በምግብ እጦት፣ እጥረትና ችግር ምክንያት ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎችን ብዙ ናቸው።

*በአጠቃላይ ባላጠፋነው ጥፋት የጦርነት ሰለባ በመሆናችን  መሞታችን፣ መቁሰላችን እና መውደማችን ሳያንስ መንግስትም ረስቶናል። (ነዋሪዎች)*

ህዝቡ በየአከባቢው ስላለው ችግር መምከር እና መወያየት የሚያስችል እድል እያገኘም አይደለም።  በተለያየ ምክንያት በማፈጠሩ የቀበሌ ስብሰባዎች የህዝቡን ሀሳብ የሚያነሳ ሰው

ሲኖር ደግሞ ከአስተዳዳሪዎቹ ምንም አይነት መፍትሄ አግኝቶ አያውቅም በሚል ነው የሚገልፁት፡፡

በዚህም ህዝቡ ሰግቶና ተሳቆ ነው እንዲኖር የተገደደው፡፡ የአከባቢው አስተዳዳሪዎች የህዝቡን ችግር ለመቅረፍ ወይም ለማቃለል የሚያደርጉት ጥረት አለ ወይ በሚል ለአከባቢው ነዋሪዎች የቀረበ ጥያቄ በሚከተለው መልኩ ገልፀውታል፡፡

> *"ጉዳያቸውም አይደለም፣ ለራሳቸው የሚሆን ጥሩ ቤት አላቸው፣ የመንግስት መኪናም አላቸው፣ ከዚህ ውጭ ስልጣን እንዳይቀሙ ያስቡ እንደሆነ እንጂ ስለህዝቡ ችግር አይ ጨነቁም ወረዳውም ለነሱ በሚመች ወደ ፋፂ ወስደው ከኛ በተሻለ የፀጥታ ሁኔታ መኖርን ነው የተመረጠው" (ከኗሪዎች አንደበት)*

ነዋሪዎች እንደሚሉት የወረዳው አስተዳዳሪዎች ዘላቂ የመፍትሄ ሀሳብ ላይ አያተኩርም፡፡ ወደ ስልጣን ሲመጡ የሚሯሯጡት የግል ጥቅማቸው ማሳደድ ላይ ነው፡፡ በዚህም የህዝቡን ሮሮ ማዳመጥም አይችሉም፡፡ **የወረዳው ምክር ቤት በሚየደርጋቸው ስብሰባዎት የህዝቡ ችግርና የልማት ጥያቄ አልፎ አልፎ የሚነሳ ቢሆንም ችግሩ የሚፈታው በሀገር ደረጃ በመንግስት ነው የሚል ምላሽ ከመስጠት ወጭ ምንም አይነት መፍትሄ አግኝቶ አያውቅም፡፡** የሚነሱት ጥያቄዎች ወደ ክልልም ይሁን ወደ ፌዴራል መንግስት ይድረስ አይድረስ ራሱ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ነው ህዝቡ የሚናገረው፡፡ በሰላማዊ ሰልፍ መልክ የፀጥታና ሌሎች ችግሮቻችሁ አሰምታችሁ ታውቃላችሁ ወይ ተብለው ሲጠየቁ፣ ይህማ፣ ጭራሹ የሚሰጠን ስንዴ ሊያስቀርብን ስለሚችልና ስለምንሰጋ አናስበውም፣ ነው የኗሪዎች ምላሽ፡፡

የጉዙአችን መጀመርያ የዛላአንበሳ ከተማ ስለነበረች ዛላአንበሳን እንደ መግብያ እና እንደማሳያ ነው እንጂ በዚህ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ያለው የትግራይ እና የዓፋር ህዝብ ላለፉት 18 አመታት ተሸክሞት እየኖረ ያለው የሀገር ችግር ግን ከዚህም በላይ የሰፋ እና የከፋ ነው፡፡ የተወሰኑትን በሚከተሉት ርእሰ ጉዳዮች ከፋፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

## 11.1. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

በነዚህ በጦርነቱ ቀጣና ውስጥ የሚገኙት አከባቢዎች ላይ የሚኖረው ህዝብ አብዛኛው ኑሮው በግብርና ስራ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ዋና መተዳደርያው የሆነው የእርሻ እና የእንስሳት እርባታ ስራው መከወን የሚችለው በአከባቢው ሰላም እና መረጋጋት ሲኖር ነው፡፡ ነዋሪው የእርሻ መሬቱ በሁለት ባላንጣ ሀገር የጦር ሀይሎች ፍጥጫ ውስጥ ሆኖ፣ በየግዜው በሚደረግ የቶክስ ልውውጥ እና በተቀበረ ፈንጂ እየሞተ እና እየቆሰለ፣ የሚያረባቸው የእንስሳት ሀብቱ እየተዘረፈ፣ በውሀ እና ግጦሽ እጦት እያለቁበት አርሶ እና አርብቶ ማልማት እና ማደግ አይችልም ብቻም ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ቀንና ለሊት ሰላም አጥቶ በጭንቅና መከራ ከመኖር ውጭ ሌላ አማራጭ የሌለው ሆኖ ወደ ሰማይ ከመፀለይ ያላለፈ ኑሮ እንዲገፋ የተገደደ ነው። ህዝቡ ሰርቶ እና በልቶ ማደር የሚችልበት በሰላም የሚያሳልፋት አንድም ቀን እንደሌለች መሬት ላይ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው፡፡ ኑሮው የብርሰትና በኑሮ ችግር አዙሪት ውስጥ የገባ ነው።

በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ያለው ሁኔታም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የጥናት ቡድኑ ተዘዋውሮ ባየባቸው ቦታዎች የታዘበው፣ ከአከባቢው ነዋሪዎች፣ ከአስተዳዳሪዎች፣ ከፀጥታ እና ከምልሻ አባላት የተገኘው መረጃ የሚያሳየውም ይህንኑ ሀቅ ነው፡፡ ለምሳሌ የኤርትራ አዋሳኝ እና በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚገኙት ከላይ በሰንጠረዥ 2 ላይ የተዘረዘሩት 12 የትግራይ ክልል ወረዳዎች የሚኖረው 1.5 ሚልየን የሚሆነው ህዝብ አብዛኛው ኑሮው በእርሻ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በነዚህ ወረዳዎች የሚኖረው ህዝብ የእርሻ መሬቱ የሚበዛው ወደ ኤርትራ ጦር ምሽግ በቅርብ ርቀት ያለ፣ በአንዳንድ አከባቢ ወደ ምሽጉ የተጠጋ በመሆኑ ለኑሮው መሰረት የሆነውን የእርሻ ስራውን በእግባቡ መስራት፣ ማልማት እና

ማምረት ያልቻለበት ሁኔታ እንደሆነ በተግባር የሚታይ ነው፡፡ የቤት እንስሳዎችም ጥዋት ወጥተው ማታ ሊመለሱ መሆናቸው ምንም ዋስትና የሌለው ነው።

ይህንን ሀቅ በትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን ላይ በጦርነቱ ቀጠና ውስጥ ካሉት ወረዳዎች የሁለቱም ማለትም የጉሎመኽዳ እና የኢሮብን ብቻ በመውሰድ በምሳሌነት ማየት ይቻላል፡፡ ጉሎመኽዳ የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ባለስልጣና በ2009 ዓ/ም ባስቀመጠው ትንበያ መሰረት 98,857 ህዝብ የሚኖርበት ወረዳ ነው፡፡ በዚህ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙት 7 ቀበሌዎች (የዛላአንበሳ ከተማን ጨምሮ) ወደ 40,000 ህዝብ ይኖርባቸዋል፡፡

*ሰንጠረዥ 7፤ በጉሎመኽዳ ወረዳ መልማት ያልቻሉና በእርዳታ የሚኖሩ ቀበሌዎችና የህዝብ ብዛት*

| ተቁ | ቀበሌ | የህዝብ ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | ሶበያ | 7,958 |
| 2. | ማርታ | 5,504 |
| 3. | አዲስ-አለም | 4,923 |
| 4. | አዲስ-ተስፋ | 4,480 |
| 5. | ሸዊተ-ለምለም | 4,911 |
| 6. | መዛብር | 3,328 |
| 7. | ዛላአምበሳ | 9,034 |
| ድምር | | **40,138** |

እነዚህ አከባቢዎች እና ነዋሪው ህዝብ በዚሁ ሰላም ጨርሶ በሌለበት አደገኛ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው የሚበዙት መደበኛው የእርሻ እና ሌሎች ገቢ ማስገኛ ስራዎች መስራት ስለማይችሉ ላለፉት ሀያ አመታት በእርዳታ እህል ለመኖር የተገደዱ ናቸው፡፡

በዚሁ ዞን በኢሮብ ወረዳ ያለው ሁኔታም ተመሳሳይ ነው፡፡ በወረዳው የኢትዮጵያ ስታስቲክስ ባለስልጣና በ2009ዓ/ም ባስቀመጠው ትንበያ መሰረት 29,374 ህዝብ ይኖራል፡፡ በዚህ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙት ቀበሌዎች በ አምስቱ ወደ 24,702 ህዝብ ይኖርባቸዋል፡፡

*ሰንጠረዥ 8፣ ኢሮብ ወረዳ ማልማት ያልቻሉና በእርዳታ የሚኖሩ ቀበሌዎችና የህዝብ ብዛት*

| ተቁ | ቀበሌ | ህዝብ ብዛት |
|---|---|---|
| 1. | አርዓ | 4705 |
| 2. | ዓሊተና | 5331 |
| 3. | ሀገረኮማ | 3988 |
| 4. | ወርዓትለ | 4631 |
| 5. | ዳልጌዳ | 6047 |
| ድምር | | 24702 |

ከላይ በሰንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው በነዚህ 5 የወረዳው ቀበሌዎች የሚኖረው 24,702 ህዝብ ለአስርት አመታት ሴፍቲ ኔት በሚል ሽፋንና በስንዴ ምፅዋት ሲማቀቁ የኖሩ ህዝቦች ናቸው፡፡ ሴፍቲ ኔት እንደ የአጭር ጊዜ መሸጋገርያ እንጂ እንደ ያንድን አከባቢ ህብረተሰብ ቋሚ የኑሮ አማራጭ ተደርጎ ለአንድ ህብረተሰብ ሲቀርብለት ሳይጋነን ይህ በትግራይ የታየ በጣም መጥፎና ህዝቡን ተመፅዋች ያደረገ፣ በስራ ራሱን ከመቻል

ያራቀ፣ ህብረተሰቡ ራሱ እንዲችልና እንዲለማ ፈፅሞ ያላደረገ በመሆኑ ፀረ ህዝብና ልማትን ወደ ጎን እንዲተው በማድረግ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰና እያደረሰ ያለ፣ ጥገኛ ማህበረሰብ የፈጠረና እየፈጠረ ያለ ነው።

ሁሉም ሰብአዊና ዴሞክርያስያዊ መብቶቹ ተመፅዋች በመሆኑ ምክንያት የተነፈገና የተነጠቀ ህብረተሰብ አማራጭ የሌለው መሆኑ አውቆ ራሱን ደፍቶ እንዲኖር ያስገደደ መሆኑ ህሊና ያለው በቀላሉ ሊገነዘበው የሚችል ጉዳይ ነው።

በዚህ ትኩረት ባጣው የጦርነቱ ቀጣና ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ላይ እያጋጠመ ያለው ሌላው ኢኮኖምያዊ ችግር የከአካባቢው ነዋሪ ሀብት የሆኑት እንስሳት ወደ ኤርትራ በተደጋጋሚ ውሀ እና ግጦሽ ፍለጋ ተሻግረው ስለሚሂዱ እና ቀልጠው የሚቀሩ መሆናቸው ነው፡፡

በበርካታ አከባቢዎች የነዋሪው የእንስሳ ሀብት ግጦሽ መሬት በዚሁ አደገኛ የጦርነት ቀጠና ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ከብቶች ውሀ የሚጠጡባቸው ኩሬዎችና ወንዞች በተመሳሳይ ሁኔታ በአብዛኛው ወደ ኤርትራ ጦር ምሽግ የተጠጉ በመሆናቸው እና ሌላ አማራጭ ውሀ የሚያጠጡበት የልማት አውታር ያልተሰራላቸው በመሆኑ ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በመረብለኸ ወረዳ የአካባቢ እንስሳ ውሃ የሚጠጡበት ጉድጓድም ይሁን ሌላ የውሃ ምንጭ ስለሌለ ወደ ኤርትራ ምሽግ ተጠግተው መረብ ላይ ነው የሚጠቀሙት፡፡

በዚህ አይነት ሁኔታ የነዋሪው የእንስሳ ሀብት ለግጦሽ እና ውሀ ለመጠጣት ወጥተው በተቀበረ ፈንጂ ያልቃሉ፣ ላይመለሱ ወደ ኤርትራ ይሻገራሉ፣ በኤርትራ ሀይሎች በሚደረግ ዘረፋም ሰለባ ይሆናሉ፡፡

የኤርትራ ወታደሮች ግመልን ጨምሮ የተለያየ የነዋሪው የእንስሳት ሀብት ዘርፈው ወስደው የሚያረቡበት እና የሚጠቀሙበት ሁኔታ ያለ መሆኑንም ማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡- መረብለኸ

ወረዳ በምትገኘው አዲቡረይ ከሚባለው ቦታ አንድ ጊዜ ብቻ 160 በጎችና ፍየሎች፣ 10 አህዮች፣ 12 ከብቶች እና 50 ግመሎች በኤርትራ ወታደሮች ተዘርፈው መወሰዳቸውና ቀልጠው መቅረታቸው ኗሪዎች ይገልፃሉ። በታጠቀው የኤርትራ ኃይል የተዘረፈ ሁብት፣ እንስሶች ወደ ኤርትራ መሬት ተሻግረው ሲሄዱ ንብረቱ ያጣው አርሶ አደር የሚያገኘው ምንም አይነት ካሣ የለም። ይባስ ብሎም ንብረቶቻችሁን መጠበቅ ነበረባችሁ በሚል ተወቃሽ እንሆናለንም ይላሉ።

ነዋሪው በዚህ ሁኔታ ከብቶቹ ሲሻገሩበት የአስተዳደር አካላት ተጠያቂ ስለሚያደርጋቸው ሄደው ማምጣት አይሞኩሩም። ምክንያቱም ከሻዕቢያ ጋር ትገናኛለህ በሚል ተጠያቂ ስለሚሆኑ እንዳይሰማባቸው እና እንዳይታወቅባቸው ዝም በማለት ቀልጠው እንደሚቀሩ ይናገራሉ።

በአካባቢው ያለው የተለያዩ የእንስሳት ዋጋ ለግንዛቤ ያህል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

*ሰንጠረዥ 9 በአካባቢው ያለው የተለያዩ እንስሳት ዋጋ*

| ተቁ | የእንስሳው አይነት | የአካባቢው አማካኝ ዋጋ በብር |
|---|---|---|
| 1. | ግመል | 16,000 |
| 2. | በግና ፍየል | ከ1,000 እስከ 3,000 |
| 3. | አህያ | 2,000 |
| 4. | በሬ | 15,000 |
| 5. | ላም | 4,000 |

*ምንጭ፤ ከአከባቢ ኗሪዎች*

ከ1990 ዓ/ም እስከ 1994 ዓ/ም ድረስ ሲጠፉ የነበሩት የእንስሳት ቁጥር የመመዝገብ ሂደት ነበር። ይሄም ሊሆን የቻለው በጦርነቱ ምክንያት የወደመ ንብረትና ሀብት ካሣ ሊከፈል ይችላል የሚል ተስፋ ስለነበር ነው በሚል ነዋሪዎች ይገልፃሉ።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታን ስለማስለቀቅ አስመልክቶ አንቀፅ 40(8) ላይ፤

*"የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግስት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ተመጣጣኝ ካሳ በቅድምያ በመክፈል የግል ንብረትን መወስድ ይችላል።"*

በማለት ይደነግጋል። ከዚህ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ለመረዳት የሚቻለው ማንኛውም ዜጋ ንብረት የማፍራት፣ ተጠቃሚ የመሆን መብት እንዳለውና ይህ የግል ሆነ የጋራ ባለንብረትነት መብት በህግ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚወሰድበት ሰው በቅድምያ ካሳ የማግኘት መብት እንዳለው የሚያረጋግጥ ነው። ይህም መሬት የመንግስትና የህዝብ ነው የሚለውን ህገ-መንግስታዊ መርህ መሰረት በማድረግ ዜጎች በመሬት ላይ በገንዘባቸውና በጉልበታቸው ስለሚሰሩት ቤት ወይም ስለሚያፈሱት ሃብት የሚኖራቸው መብት የባለቤትነት መብት በመሆኑ ለዚህ የግልም ሆነ የጋራ ንብረት ካሳ የማግኘት መብታቸውን በማስመልከት የሚደነግግ ህግ ነው። ካሳ ይከፈለኝ ብለው በልበ ሙሉነት እንዲከራከሩ የሚያስችላቸውም ነው። የአቅማቸውን ያህል በመሬቱ ላይ ኢንቨስት እንዳያደርጉ፡ ጉልበታቸውን፤ ጥረታቸውንና እውቀታቸውን እንዳያፌሱ፣ ከሚኖር ስጋት ተላቀው ህግ-መንግስትና እሱን መሰረት በማድረግ የወጡ ሕጎች ዋስትና ሰጪነታቸውን ተገንዝበው የልማቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው ነው።

በተመሳሳይም ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከመሬት ባለይዞታነት ማስለቀቅን በሚመለከት በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 በአንቀፅ 7(3) ላይ፡-

*"የገጠር መሬት በላይዞታነት ለህዝብ ጥቅም ሲባል መሬቱን በመንግስት እንዲለቅ ሲደረግ በመሬቱ ላይ ላደረገው ማሻሻያና ላፈራው ንብረት ተመጣጣኝ ካሳ ይከፈለዋል። ወይም ለለቀቀው መሬት ምትክ በታቻለ መጠን ሌላ ተለዋጭ መሬት እንዲያገኝ ያደረጋል" ይላል።*

በዚህ የጦርነት ቀጠና አከባቢ በርካታ የአከባቢው አርሶ አደሮች መሬት፣ እና ህብረተሰቡ በጋራ ይጠቀምባቸው የነበሩ የግጦሽ መሬት ምሽግ ተሰርቶባቸዋል፣ የጦር ካምፕ ሆነዋል። በዚህም ምክንያት አንዳንድ አከባቢዎች ላይ ለተነሺ አርሶ አደሮች መጠኑ አጥጋቢ ባይሆንም ካሳ የተከፈለበት ሁኔታ ቢኖርም ወጥነት ባለው መልኩ በሁሉም አከባቢ ለሁሉም ተነሺዎች ካሳ ያልተከፈለ መሆኑን ግን የአከባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ።

ለምሳሌ፡- በትግራይ ማእከላዊ ዞን አሕፈሮም ወረዳ ላይ ዓዲጨጓር በሚል በሚታወቀው አካባቢ ያሉ ተነሺ ነዋሪዎች እንደሚገልፁት በአካባቢው ካሣ የሚባል ነገር አልተሰጠም።

ካምፕ የሚሰራባቸው አካባቢዎች የሚመርጠው መከላከያ ነው። በዚህ ሁኔታ የግጦች ቦታዎች በብዛት ይያዛሉ። እነዚህ ቦታዎች የመንግስት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ካሳ አይታሰብም። ምሽግና ካምፕ ለመገንባት ግብአት ላይ የሚውለው ድንጋይ፣ እንጨት፣ አሸዋና ሌሎች የአካባቢው ነዋሪዎች ሀብቶች ቢሆኑም ከሰማይ እንደተሰጠ መና ይቆጠራል እንጂ ያካባቢው ህብረተሰብ የጋራ ንብረት እንደሆነ ታሳቢ አይደረግም፣ ማካካሻም አልተደረገለትም እንደ ያካባቢው አርሶ አደሮች አገላለፅ። ሰራዊቱ በየግዜው ሲለማመድ በታንክ እንቅስቃሴና በቶክስ የሚፈጀው እፀዋት፣ሳርና ግጦሽ በጋራ ባካባቢው ለሚኖረው ህብረተሰብ የሚፈጥረው ጫና ምንም ግምት የሚሰጠው ጉዳይ እንዳልሆነ መረዳት ተችሏል።

በመሰረቱ ይህ በጦርነት ቀጠናው የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል የደረሰበት የኢኮኖሚ የከፋ መንሳቀል ባከባቢው ካለው የኢትዮጵያ እና ኤርትራ ወታደራዊ ፍጥጫ ከአስርት አመታት የጊዜ ሁኔታ ጋር አያይዞ ለማየት የዳሰሳው የትኩረት አከባቢ ስለሆነ ካልሆነ በስተቀር በመሰረቱ

በትግራይ ደረጃ ያለውን የእድገት ሁኔታ ጋር ሲታይም ከነጭራሹ ተነጥሎ ላይታይ ይችላል። በሀገር ደረጃ ካለው ሁኔታና ለውጥ በማገናዘብ ትግራይ ላይ ከደርግ ውድቀት በኃላ ያለፉት 5 እና 6 መርሀ ግብሮችና ውጤቱ ሲታይ አሁንም ድህነቱ ስር የሰደደ እንደሆነ ከተለያዩ የስታስቲክስ መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል።

ከ 27 ዓመት የደርግ ውድቀት በኃላ አሁንም ከሌላው የሀገራችን አከባቢ በተለዬ ትግራይ ከ 27% ህዝብ ከድህነት ወለል በታች ነው። ትግራይን በብቸኝነት የተቆጣጠረው ድርጅት ህወሓት ግን፣ ጀርመኖች ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃት በኃላ በአስር አመት ውስጥ በጦርነቱ ምክንያት ጭራሹን ወድሞ የነበረው ኢኮኖሚያቸውን ተአምር በሚያስብልና ከጀርመን በተናነሰ ወድመው ከነበሩት ከነ እንግሊዝ እና ፈረንሳይ ከኃላ ተነስተው አልፈው ሀገራቸውን መገንባት ችሏል። ይህንን እውነታ ህወሓት በሰነድ ዘግቦ ሲያበቃ ከ 27 አመታት በኃላ ትግራይ ላይ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲታይ ግን የውሀ ሽታ ሆኖ የቀረ በመሆኑ ለምን ታድያ የጀርመንን ልምድ መቀመርና መዘገብ አስፈለገ ያስብላል።

ደርግ እንደተደመሰሰ ከጥቂት አመታት በኃላ ትግራይ ላይ ሳርት የሚባል ድርጅት ተመስርቶ እንደነበር የሚታወቅ ነው። የሳርት ዋና ስራም ከውሀ እና መስኖ ልማት የተያያዘ ሆኖ፣ በጊዜው በትግራይ ብቻ ከ 500 የማያንሱ ግድቦችን ይሰራሉ ተብሎ ስለነበር ተስፋ የተደረገበት ጉዳይ ነበር። በኃላ ግን ግድቦቹ የት ገቡ ሲባል ትግራይን የማልማት የህወሓት ቁርጠኝነት ያጣው ከጥዋቱ ነው፣ ብሎ እውነታውን ግልፅ ከማድረግ ይልቅ፣ ከዚህ ግባ የማይባልና፣ ከደርግ ውድቀት በኃላ የትግራይ ህዝብ ህልም ምን እንደነበረና እንደሆነ፣ ያ ሁሉ ዋጋም ህዝቡ ለምን እንደከፈለ ጆሮ ዳባ ብሎ፣ የሆነ ያልሆነ መልስ ለመስጠት፣ አውቃለሁ የሚል ሁሉ ትክክለኛውን መልስ ከመስጠት ይልቅ ዳር ዳር ሲል ይታያል።

## 11.2. ማሕበራዊ ሁኔታ

በቀጠናው ያለው የማህበራዊ አገልግሎቶች ያየን እንደሆነም በሁለት አመቱ የለየለት የጦርነት ወቅት በርካታ የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች መንገዶች እና ሌሎች የልማት አውታሮች ገና መልማት ሳይጀምሩ በጦርነቱ ምክንያት ወድመዋል። በዚህም አከባቢው ቀድሞም ቢሆን በትጥቅ ትግሉ እና ከዝያም በፊት የተጎዳ እና በልማቱ ወደኃላ የቀረ በመሆኑ ለከፋ ችግር አጋልጦታል። ከሁለቱ የጦርነት አመታት በኃላ እና በአስራ ስምንት የቀዝቃዛ ጦርነት ጊዜ ውስጥ ምንም የሚታይ ወይም ትርጉም ባለው ግልጋሎት የሚሰጥ ተቋም አይታይም። ያሉትም በሰላም እጦት ምክንያት የችግሩ ሰለባ የሆኑ ናቸው።

በነዚህ የኤርትራ አዋሳኝ በሆኑት አከባቢዎች የሚኖረው ህዝብ በማህበራዊ አገልግሎቶች ላይ የሚነሳው ሌላው ችግር በአከባቢው የሚመደቡት የጤና፣ ትምህርት፣ እርሻ እና ሌሎች ባለሙያዎች ብቃት እና ልምድ የሌላቸው መሆናቸው እና አንዳንዴም ከሌሎች አከባቢዎች በቅጣት ተዛውረው የሚመጡ ስለሆኑ ባሉት የልማት አውታሮች የሚሰጠው አገልግሎትም ከነጭራሹ የሰው ጥራት የጎደለው መሆኑን ነው ህብረተሰቡ በምሬት የሚገልፀው። ይህንን ጉዳይ አስመልክተን በየቦታው ላሉ የአስተዳደር አካላትን ጠይቀን ባገኘነው መረጃ መሰረት ያረጋገጥነውም የህዝቡ ጥያቄ ትክክለኛ እና እውነታውን የሚያንፀባርቅ መሆኑ ነው። ያነጋገርናቸው የአስተዳደር አካላት የችግሩ ምንጭ፣ በነዚህ የኤርትራ አዋሳኝ በሆኑት ወረዳዎች እና አከባቢዎች እንደ መንገድ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ መብራት፣ ውሃ እና ሌሎች መሰረታዊ የልማት አውታሮች የሌሉ በመሆናቸው እና ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት ብቃት ያለቸው የመንግስት ሰራተኞች ወደ እነዚህ አከባቢዎች ሂደው ለመስራት ፍቃደኛ ስለማይሆኑ ነው የሚል ነው። በሌላ በኩል ግን መንግስት እንደዚህ አይነት ችግር ባለባቸው አከባቢዎች ለሚመደብ የመንግስት ሰራተኛ

ትኩረት ሰጥቶ ልዩ ድጋፍ እና ማበራተቻ ባለማድረጉም ጭምር የተከሰተ ችግር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ሁኔታውን የሚመጥን ፖሊሲ መከተልን ይጠይቅ ነበር ማለት ነው፣ መስተዳድሩ የህዝቡን ችግር የማቃለል ዓላማ ቢኖረው።

በሌላ መልኩም እነዚህ አከባቢዎች የነበሩት የልማት አውታሮች ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስችል መልኩ በጦርነቱ ምክንያት ወድመዋል። ለምሳሌ መንገድን የወሰድን እንደሆነ ወረዳን ከወረዳ ቀበሌን ከቀበሌ የሚያገናኙ አዳዲስ መንገዶች አልተሰሩም ከጦርነቱ በፊት የነበሩት የተወሰኑት ደግሞ ተቆፋፍረው ከጥቅም ውጭ ሆኖዋል። በዚህም ወደሚበዙት የኤርትራ አዋሳኝ አከባቢዎች ገብተው የሚሰሩ እና ህዝቡን የሚያገለግሉ የመጓጓዣ አግልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የሉም። እዚህ ላይ በተለይ በትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን የምትገኘውን የኢሮብ ወረዳ ላይ ያለውን የመንገድ ችግር ሳይጠቀስ አይታለፍም። ወረዳዋን ከዋናው የአድግራት መስመር ማገናኘት የሚችለውን መንገድ ያልተሰራ እና ያልተጠገነ በመሆኑ የወረዳው ህዝብ ሃያ አመት ሙሉ ለብቻው ተነጥሎ የጦርነት ቀጠና ደሴት ውስጥ እንዲኖር እና መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት በሌለበት ሁኔታ ሆኖ ከባድ ፈተና ላይ እንዲወድቅ ተደርጓል።

ህብረተሰቡ የሰላም እጦት ችግር ከሚፈጥርበት ከባድ የሂወት ፈተና በተጨማሪ በኢኮኖሚው ክፉኛ የተጎዳ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለውም በስንዴ ምፅዋት የሚኖር፣ ሂወቱ በሞትና በመኖር የተቀረቀረች፣ ኑሮው ከሰራዊትና ከቶክስ ጋር ሆኖ እያለ፣ ይባስ ብሎም ከዚህ ግባ የሚባል ማህበራዊ ግልጋሎት፣ ለምሳሌ የትምህርትና የጤና አገልግሎት የሌለው ወይም ፍፁም ጥራት የጎደለው ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ሲታይ የህዝብ ችግርን መፍታት በሚጠየፍ አመራር ስር ወድቆ ለመገመት የሚያስቸግር ዋጋ እየከፈለ እንዲኖር የተገደደ እንደሆነ፣ በሁሉም ዘርፍ አፍ አውጥቶ ህብረተሰቡ የሚናገረው ጉዳይ ሆኖ ይገኛል።

ለምሳሌ ባካባቢው ያሉት ህፃናት (ወጣቶች) እና የትምህርት ሁኔታ ሲታይ፣ ልጆች ስለ ትምህርት ደረጃቸው አንደኛ - ሁለተኛ- ሶስተኛ ወዘተ ከማለት ባካባቢው ስላሉ የክፍለ ጦሮች መጠርያ፣ ሀያኛ - ሀያ ሁለተኛ - ሳላሳ አንደኛ ወዘተ እንዲሁም የብርጌዶች፣ ሻለቃዎች መጠርያ ቁጥርና ታንከኛ፣ መድፈኛ፣ ሻለቃ፣ ብርጌድ ወዘተ እያሉ መጥራት ይቀላቸዋል። አከባቢው የጦር ካምፕ እስከሆነና ሰላም በሌለበት መስተዳድሩ ይህ ሁኔታ ለህብረተሰቡ የሚፈጥርበት ጫና ታሳቢ አድርጎ፣ ጫናውን የሚቀንስ ፖሊሲና ተግባር በሌለበት፣ ህፃናትና ወጣቶች ቀለም ሳይሆን የሚያጠኑት የክፍለ ጦሮችና የብርጌዶች መጠርያ፣ ታንክና መድፍ ወዘተ የሚለው በጭንቅላታቸው እየፃፉ ባክነው ይቀራሉ። ከቀን ተቀን ሂወታቸው ጋር ለሀያ አመታት የዘለቀው የተለያዩ የወታደር ጠመንጃ፣ ወታደራዊ ተሽከርካሪ፣ የወታደር ዩኒፎርም ወዘተ ነው። ሌላ ነገር የለም።

## 11.3. ስነልበናዊ ሁኔታ

ትራውማ (Trauma) የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ከግሪክ የመጣ ሲሆን የውስጥ የስነ ልቦና ስብራት ወይም የመንፈስ ቁስል የሚል ፅንሰ ሀሳብ የያዘ ቃል ነው። ትራውማ በእጅ የማይዳሰስ በአይን የማይታይ የውስጥ ህመም ነው። ትራውማ በአንድ ጊዜ ወይም ለአጭር ጊዜ በደረሰ አደገኛ ክስተት ወይም ሁኔታ ምክናያት ህመሙ ሊጀምር ይችላል። በአንዳንዶች ላይ በተደጋጋሚ እንደዚህ አይነት ጉዳት ሲደርስባቸው በዚያ የስሜት ስብራት ሊመጣባቸው ይችላል፣ ለምሳሌ ጦርነት በሚካሄድበት ቦታ የሚኖሩ ሰዎች የህሊና ቁስል ሊፈጠርባቸው እንደሚችል የስነልቦና ምሁራን ይገልፃሉ። በግጭት፣ ውግያዎች ማቋረጫ በሌለበት የሰላም እጦት ምክንያት በሂደትና በሂወት ጉዟቸው ውስጥ በሚገጥማቸው ህሊናን፣ ስብእናንና ሞራልን በሚጎዱ ክስተቶች ጭንቅላታቸው ይጎዳል፣ ሙሉ ሰው ሳይሆኑ ጎዶሎነት ያላቸው ይሆናሉ።

በዚህ የኤርትራ አዋሳኝ አከባቢዎች የሚኖረው ህዝብ በየጊዜው በሚያጋጥመው የተኩስ ልውውጥ ላለፉት ሀያ አመታት ሙሉ በከፍተኛ የስነልቦና ጫና ላይ ሆኖ ነው የኖረው፡፡ ተማሪዎችም ተረጋግተው መማር የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡ በየጊዜው በሚከሰት የቶክስ ልውውጥ የአካባቢው ነዋሪዎች ይሞታሉ ይቆስላሉ። ይህም ህዝቡ ለማያቋርጥ የአእምሮ ጭንቀት እንዲዳረግ አድርጎታል። በተለይ በዚህ አከባቢ በሚኖሩ ህፃናት፣ ሴቶች እና አዛውንቶች ላይ ያደረሰው ተጽኖ ደግሞ የከፋ ነው፡፡

በጦርነቱ ምክንያት ለበርካታ አመታት በእንደዚህ አይነት የስነልቦና ጫና ላይ የሚኖር ህዝብ ታድያ፣ በዚህ ዙርያ የሚደረግ ራሱን የቻለ ልዩ የስነልቦና ሙያዊ ጥናት ማድረግ የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ለከፍተኛ የውስጥ የስነ ልቦና ስብራት ወይም የመንፈስ ቁስለት ትራውማ (Trauma) የተዳረገ ህብረተሰብ እንደሆነ ግን መሬት ላይ ያለውን ሀቅና ለአስርት አመታት ህዝቡ ያሳለፈውና ተሸክሞት ያለ ሰቆቃ በማየት መገንዘብ ይቻላል።

## 11.4. ፖለቲካው ሁኔታ

ሰላም ካለ ልማት፣ ሰርቶ መብላት እና እድገት አለ። ሰላም ሲኖር ህዝቡ በሰላም ወጥቶ እንደሚገባ ስለሚያውቅ ያለስጋት የመንግስት ልዩ ትኩረት እና ድጋፍ ሳይሻም በጥረቱ ኑሮውን ማሸነፍ ይችላል።

በትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን የምትገኘው እንዳ አብርሃ ወአፅብሃ ቀበሌ ከጦርነት ቀጠናው ርቀው ከሚገኙ የክልሉ ጣብያዎች አንድዋ ነች። በዚህ ቀበሌ የተሰራው ተፈጥሮን የማዳን ስራ አመርቂ ውጤት አስገኝተዋል። ክረምት በገባ ቁጥር ከጋራ እና ሸንተረር የሚወረድ ጎርፍ ከተራራው በታች ላሉ ማሳዎች ከጥቅም ውጭ ሲያደርግ ለዘመናት ቆይቷል። አሁን ግን በዚሁ ሰላም በሰፈነበት ቀበሌ ኖዋሪዎች ተፈጥሮን አሸንፈው

ተፈጥሮን የማዳን ስራ በመስራታቸው ማሳው በመስኖ ለምቷል፣ ተራሮች የዱር እንስሳት ጥላ ሆኖዋል።

በዚህ አከባቢ የሚኖረው ህዝብ ባለፉት ሀያ አመታት ከጦርነት ቀጠናው በተነፃፃሪ ራቅ ብሎ የሚገኝ በመሆኑ፣ ያገኘውን አንፃራዊ ሰላም ተጠቅሞ መልማቱ የሚያስደስት ነው። በዚህም ምክንያት ብዛት ያላቸው ጎብኝዎች ደርሰውባታል። በሀገር በቀል እና ዓለም አቀፍ የእርዳታ እና የልማት ድርጅት ተወካዮች እና በአለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሀን ተጎብኝታለች። ጎብኝዎች ይህችን ጣብያ ብቻ ጎብኝተው ስለሚመለሱ ግን ትግራይ በሞላ እንደ አብርሀ አፅብሀ አይነት ሁኔታ ያላት ይመስላቸዋል።

በጣብያዋ ያለው ልማት በቅን ልቦና ሲታይ፣ እሰዮው የሚያስብል ነው። በሌላ በኩል ግን በኤርትራ እና ኢትዮጵያ ጦርነት ምክንያት ላለፉት ሀያ አመታት የጦርነት ቀጠና ሆነው በቆዩት አከባቢዎች እና ህዝቡ ግን የዚህ ሀገራዊ ችግር ሰለባ መሆኑ፣ በሰላም እና መረጋጋት እጦት፣ መሞቱ መቁሰሉ እና በድህነት መሰቃየቱ ሳያንሰው፣ ሊደገፍ ሊዶጎም እና ችግሩ ከሚገባ በላይ እንዳይሆን ማድረግ ሲገባ በፌደራል እና በክልሉ መንግስት ተረስቶ ጠያቂ እና አይዞህ ባይ ያጣ መሆኑ ነው እጅግ አሳዛኝና አጠያያቂ የሚያደርገው። እንደ የአከባቢው ኗሪዎች አባባል፣ የመገናኛ ብዙሀን ወደ አካባቢው እንዳይሄዱና እንዳይዘግቡ የተከለከሉ እስኪመስል፣ መዘገብ ይቅር ህብረተሰቡም አያውቃቸውም። ሳት ብለው ከመጡም በቴሌቪዥን ይሁን በሬድዮ እንዳይተላለፍ ይደረጋል ይላሉ።

በነዚህ የጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖረው ህዝብ የመንግስት ትኩረት ከማጣቱ በተጨማሪ የበርካታ የመልካም አስተዳደር ችግርና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሰለባም ነው።

የኢትዮጵያ ሕገመንግስት አንቀጽ 29 ላይ የአመለካከት እና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት ላይ እንደተደነገገው፣

*ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል፡፡*

በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ታድያ ባለፉት 18 ዓመታት የተሸከመውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዲታወቅለት እና እንዲፈቱለት ሀሳቡን የሚገልፅባቸው የመገናኛ ብዙሀን ማግኘት የሚችልበት እድልም ጭምር ነው የተነፈገው።

ጥናት በተካሄደባቸው አከባቢዎች የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው ከጦርነቱ በኃላ ማንኛውም የመንግስት ወይም የግል (የፌደራልም ይሁን የክልል) የመገናኛ ብዙሃን በዚህ የጦርነት ቀጠና ተገኝተው የህዝቡን ችግሮች የዳሰሱበት እና የዘገቡበት ሁኔታ የለም። በማወቅ ይሁን ባለማወቅ፣ ወይም ችግሩ የፈጠጠና ዘርፈ ብዙ እና አስጠያቂም ሊሆን ስለሚችል እንዲዳፈን ለማድረግ፣ ምክንያቱ ለመረዳት በሚያስቸግር መልኩ መገናኛ ብዙሃን ከአከባቢው የራቁ ናቸው። ይህንን ጉዳይ አስመልክተን ለትግራይ ክልል የመገናኛ ብዙሀን አጀንሲ የስራ ሀላፊዎች ጠይቀን ያገኘነው መረጃ እንደሚያረጋግጠውም፣ የክልሉ ሚድያ በዚህ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ስላለው ህዝብ እና ስላለው ችግር ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራበት ሁኔታ እንዳልነበረ ነው። ለዚሁ የሚሆን የውስጥ የአሰራር ደንብና የዘጋቢዎች ስምሪት እንደሌለ፣ ይህ ባለመደረጉም ህብረተሰቡ ስለችግሩ የሚዘግብለት አጥቶ እንደተጎዳ መረዳት ተችሏል። ሚዲያው ያለውን ክፍተት እና የህዝቡን ችግር ተገንዝቦ ችግሮች እንዲፈቱ ድምፅ መሆን ሲገባው ችግሩ የሚፈታው መንግስት በሚያወጣው ፖሊሲ ስለሆነ ከመንግስት የተሰጠን አቅጣጫ ደግሞ ስለሌለ ሽፋን መስጠት አልቻልንም በማለት ህዝቡ በነዚህ በህዝብ እና በመንግስት ገንዘብ የሚንቀሳቀሱት የመገናኛ ብዙሃንም እንዳይገለገል፣

እየደረሰበት የነበረና ያለ ከባድ ከሰላም እጦት ጋር የተያያዙ ውስብስብ ችግሮች ባካባቢው ብቻ ታጥረው እንዲቀሩ የሚያደርግ ከባድ ጥፋት በህዝቡ ላይ እንዲፈፀም ያደረገ አካሄድ ነው።

በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ያሉበት ችግሮች እንዳይታወቁ እና ታፍነው እንዲቆዩ ካደረጉት ጉዳዮች ሕገ-መንግስታዊ መብት የሆነው ሀሳቡን በመገናኛ ብዙሀን የመግለጽ ነፃነት መነፈጉ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሀሳቡን በነፃነት የሚገልፅባቸው መንገዶችም ስለተዘጉበት ጭምርም እንደሆነ ያካባቢው ህብረተሰብ በቁጭት የሚገልፀው ጉዳይ ነው።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 30 ላይ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብትን አስመልክቶ እንደተደነገገው፤

*ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ይላል*

ይህ መሰረታዊ ነፃነትንም ቢሆን ነዋሪው ላይ የተለያየ ተፅእኖ በመፍጠር ተግባራዊ እንዳይደረግ እና እንዲጣስ የተደረገበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህንን እውነታ አንድ የዛላአንበሳ ነዋሪ አዛውንት የገለፁት እንደሚከተለው ቃል በቃል የተቀመጠውን አረፍተነገር በማየት የችግሩ ስፋት ለመገንዘብ ያስችላል፡፡

*በምፅዋት የሚኖር ህዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጋል ብሎ ፍጹም የማይታሰብ ነው፡፡ እንዲህ ብናደርግ የሚሰጡን የእርዳታ እህል ይከለክሉናል። በዚህም በርሃብ እናልቃለን የሚል ስጋት አለን፡፡ ሰለፍ ይቅርና በሀሳብ ደረጃ እንኳ ስላለው ችግር የሚያወራ ሰው ሲገኝ አስተዳዳሪዎቹ ጠግቦ ነው፣ የሚሰጠው እርዳታ ይቀነስ ወደ ሚል ጭካኔያዊ ውሳኔ ነው የሚደርሱት፡፡ ስለዚህ ህዝቡ ሀሳቡን በነፃነት መግለጽ አይችልም፡፡*

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀጽ 50 ቁጥር 3 ላይ እንደተደነገገው የፌደራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው። ተጠሪነቱም ለሀገሪቱ ሕዝብ ነው። የክልል ከፍተኛ የሥልጣን አካል የክልሉ ምክር ቤት ነው፤ ተጠሪነቱም ለወከለው ክልል ሕዝብ ነው ይላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በህገመንግስቱ አንቀጽ 54 ቁጥር 4 ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ተጠሪነትን አስመልክቶ እንደተገለፀው የምክር ቤቱ አባላት የመላው ሕዝብ ተወካዮች ናቸው፡፡ ተገዥነታቸውም፤

ሀ) ለሕገ መንግሥቱ፤

ለ) ለሕዝቡ፤ እና

ሐ) ለሕሊናቸው፤ ብቻ ይሆናል ይላል፡፡

በዚህ የጦርነቱ ጦስ ውጤት የሆነውን ችግር 18 ዓመት ሙሉ የተሸከመው ህዝብ ጉዳይ ታድያ እነዚህ የሀገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን አካል የሆኑት የፌደራል እና የክልል ምክር ቤቶችም ጭምር የዘነጉት እና ጭራሽ ጀሮ ዳባ ያሉት እንደሆነ ነው ህብረተሰቡ የሚገልፀው፡፡

ከታች በወረዳ እና በዞን ያሉት ምክር ቤቶች እና የአስተዳደር አካላት ችግሩ ሊፈታ የሚችለው በክልል ብሎም በፌደራል መንግስት በኩል በሚቀረፅ ፖሊሲ እና በሚቀመጥ አቅጣጫ ነው በሚል የህብረተሰቡን ችግር ለመፍታት አልሞከሩም ከአቅማቸው በላይ እንደሆነ አስበው ከላይ መጠበቅ ነው ብለው የተዉት ጉዳይ እንደሆነ በያከባቢው በታችኛው እርከን ያሉ አመራሮች የሚገልፁት ነው።

ከላይ ያሉት የፌደራል እና የክልል የህዝብ ተወካዮች ምክርቤቶችም ቢሆኑ በዚሁ የጦርነት ቀጠና ውስጥ ስለሚገኘው ህዝብ፣ በጦርነቱ ምክንያት እየደረሰበት ስላለው ሶቆቃ አጀንዳ ይዘው የመከሩበት እና መፍትሄ የሰጡበት አንድም ቀን እንደሌለ የአደባባይ ሚስጢር ነው፡፡ ያነጋገርናቸው የምክርቤት አባላት ያረጋገጡልን ሀቅም ነው፡፡

ህዝቡም መፍትሄ ሊሰጡት ይገቡ የነበሩ በእነዚህ ከፍተኛ የስልጣን ባለቤት የሆኑት ምክርቤቶች እና አባል የሆኑት የህዝብ ተወካዮች ላይ ተስፋው ተሟጦ ያበቃበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው በህዝብ ተወካዮች የተቋቋመ ነው ለሚባለው የትግራይ ምክርቤት፣ ህዝቡ በራሱ ተነሳሽነት የያካባቢውን ተወካዮችን በመምረጥ እየላከ ጥያቄ የሚያቀርብበት ሁኔታ እና ጥረት እንደነበርና ይህም ውጤት እንዳላመጣ ይናገራሉ፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ ህዝቡ ተወካዮችን በራሱ መንገድ እየመረጠ ይጠይቀናል የሚለው ሀሳብ የነገሩን (ምክርቤቱ ላይ የተቀመጡት በህዝብ ውክልና መሆኑን በመዘንጋት) ያነጋገርናቸው ተመራጭ እና የምክርቤቱ አባል መሆናቸው ነው፡፡

ህብረተሰቡ ካለበት የሰላም እጦት፣ ለመገመቱ የሚያስቸግር ድህነትና የኑሮ ችግር፣ ለአስርት አመታት የዘለቀ ተመፅዋችነት እና የዚህ ውጤት የሆነው የሞራልና የስነልቦና ስብራት በተጨማሪ በክልሉ ባለው እስከ አንድ ለአምስት ደረጃ ላይ የደረሰ መዋቅርና አደረጃጀት ተጠፍሮ የተያዘና መፈናፈኛ ያጣ ህብረተሰብ ነው። እንደ ህብረተሰቡ አገላለፅ ከሆነ የመስተዳድር መዋቅሩ ከክልል እስከ ታች ጣብያ የወረደ ሆኖ በጣብያ በአንድ ለአምስት ጠፍሮ የያዘ ነው። በከተማም ይሁን በገጠሩ ይህ ነው የሚባል ሂወት በሌለውና በሰላም እጦት እየተሰቃዬ ያለው በኤርትራ አዋሳኝ አከባቢዎች የሚገኘው ህብረተሰብም ጭምር ሲሆን መዋቅሩም ከላይ እስከ አንድ ለአምስት ብቻም ሳይሆን ከክልል እስከ ታች ጣብያ ዋህዮ ጨንፈር በሚል ጎን ለጎን ከመስተዳድራዊ መዋቅሩ ጋር ወርዷል። በቀበሌ

ደረጃም የህወሓት ጨንፈሮች አሉ ይላሉ። የነዚህ የቀን ተቀን ስራቸው ምንድን ነው ተብለው ሲጠየቁ አንድ ለአምስት፣ በየቀኑ የአፈር፣ ግድብ ይሁን ሌላ ስራ እንድንሰራ ያዘናል። ወደ ግላችን ስራ ያለ አንድ ለአምስት አደረጃጀት ሀላፊ ፍቃድ መነቃነቅ አንችልም። ከአከባቢያችን ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ እንኳ ማሳወቅና ማስፈቀድ የግድ ነው። በጣም መፈናፈኛ ያሳጣን አደረጃጀት ነው ይላሉ። ነዋሪዎቹ ስለ ድርጅቱ ዋህዮ፣ ጨንፈር ስራና አደረጃጀት ሲገልፁ ደግሞ፣ እነሱ ጆሮ ናቸው፣ ማን ስለ ድርጅቱ ምን አለ? ድርጅቱን በህሜት የሚያነሰው ማን ነው? እያሉ መከታተል፣ ማሳደድና ማሸማቀቅ ነው ስራቸው ይሉና ሁለቱ ጎን ለጎን ለአስርት አመታት እየሰራ ያለው የመስተዳደርና የድርጅቱ መዋቅር ተቀርቅረንና ታፍነት መፈናፈኛ አጥተናል ይላሉ። ለነፃነት፣ ዴሞክራሲና ፍትህ የታገለ ህዝብ ለከፈለው ዋጋ ትርፉ ይህ ሆኗል ማለት ነው። ድህነት፣ ሰላም ማጣት እና ፍፁም መፈናፈኛ በሌለው አስተዳደራዊና የድርጅት መዋቅር አፈና ተቀርቅሮ መሰቃዬት።

## 12. የፌደራል እና የክልሎቹ መንግስታት ችግሩን ለመፍታት (ለማቃለል) ያደረጉት እንቅስቃሴ

በዚህ የጦርነት ቀጠና ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ችግር ዘርፈ ብዙ ቢሆንም ችግሮች ለመፍታት በፌደራል ይሁን በክልል መንግስት በኩል የተወሰደ እርምጃ እና ለሁኔታው የሚመጥን ፖሊሲም ሆነ ሌላ ተግባራዊ ምላሽ ግን ላለፉት አስራ ስምንት አመታት ምንም እንደሌለ ነው። የክልሉ መንግስት ጉዳዩ ሀገራዊ ስለሆነ መፍትሄውም በፌደራል መንግስት ነው የሚመጣው በሚል ከመጠበቅ ውጭ ሌላ ያደረገው የለም። የፌደራል መንግስትም ቢሆን ያስቀመጠው ችግሮችን ሊያቃልል የሚችል እንቅስቃሴ ይሁን የፖሊሲ ሀሳብ ምንም እንደሌለና እንዳልነበረ መሬት ላይ ወርዶ ሀቁን በማየትና ህብረተሰቡን በማነጋገር በቀላሉ

መረዳት ይቻላል። በቅንጅት ይሁን በተናጠል የህብረተሰቡን ሰቆቃ ለመረዳትም ሆነ ችግሩን በትንሹም ቢሆን ለማቃለል የተደረገ ነገር የለም።

በአከባቢው ሰላም እንዲነግስ የሚያስችል ፖሊሲን በመከተል ችግሩን በዘለቄታው መፍታት እስከሚቻል ድረስ በነበረው ሂደት፣ የክልሎቹ እና የፌደራል መንግስት የህብረተሰቡን ችግሮች ሊያቃልሉ የሚችሉ እርምጃዎች መውሰድ ባለመቻላቸው ደግሞ የህዝቡ ችግር ከባድ እንዲሆን አድርጎታል።

የፌደራል መንግስት ይህንን በጦርነቱ ምክንያት ኢኮኖሚውና ማህበራዊ አገልግሎቱ የዳሸቀውን አከባቢ ለመደገፍ እና የልማቱ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል እና ችግሩን ግምት ውስጥ ያስገባ የበጀት ድልድል እና ቀመር ያልተከተለ መሆኑ ሌላው ህዝቡን ኩፉኛ እንዲማቅቅ ያደረገው ጉዳይ ነው። ከክልሉ ፕላን እና ፋይናንስ ቢሮ ያገኘነው መረጃ  እንደሚያስረዳው ቀደም ሲል የነበረው የፌደራል መንግስት የክልሎች የበጀት ቀመር ላይ ጦርነትን ታሳቢ የሚያደርግ ራሱን የቻለ መለክያ ባይኖርም ክልሎች ከአጎራባች ሀገሮች ጋር ያላቸውን ወሰን ግምት ውስጥ በማስገባት ይፈቅድ የነበረውን በጣም ትንሽ የተጨማሪ በጀት የነበረ ቢሆንም አንደኛ በነዚህ አከባቢ ያለው ውድመትና ሰቆቃ ግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም፣ በሂደትም ጨርሶ መቅረቱ ነው መረጃው የሚጠቁመው።

ክልሉ በራሱ ያዘጋጀው እና በስራ ላይ ያለው የበጀት ቀመርን ያየን እንደሆነም እነዚህ የኤርትራ አዋሳኝ የሆኑት አከባቢዎች የጦርነቱ ሰለባ በመሆናቸው እና ልዩ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ግምት ውስጥ ያላስገባ እና የዘነጋ በመሆኑ የህዝቡን ኑሮ የከፋ እንዲሆን አድርጎታል።በአፋር ክልል ያለው ሁኔታም እንደ መረጃው ከሆነ ተመሳሳይ ነው።

በአጠቃላይ በእንደዚህ አይነት ችግር ውስጥ ያለን ህዝብ ልዩ ድገፍ ሊደረግለት እና ሊዶጎም ሲገባው ተረስቶና ትኩረት አጥቶ አስራ ስምንት የሰቆቃ አመታትን እንዲያሳልፍ የተገደደ ህዝብ ነው የሆነው። የሌሎች ለምሳሌ የደቡብና የሰሜን ኮርያ ለአመታት የዘለቀ ፍጥጫ እንዲሁም በእስራኤልና በሶርያ አዋሳኞችም እስከ ቅርብ ጊዜና ሶርያ እስክትፈርስ ጊዜ ያለውን ሁኔታ ለማነፃፀርያ ማየት ይቻላል፣

ዶቡብ ኮርያ ከሰሜን ኮርያ በምትዋሰንባቸውና የጦርነት አደጋ ባንዣበበበት አከባቢ የሚኖር ህዝቧ የኑሮና የእድገት ደረጃ ሲታይ፣ የደቡብ ኮርያ መንግስት በሚከተለው ፍትሀዊና የጠረፉን እውነታ ግምት ውስጥ ያስገባ ፖሊሲና ተግባር ምክንያት ባካባቢው የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል በሰላም እጦት ምክንያት በህብረተሰቡ የሚደርሰው የኢኮኖሚም ሆነ ሌሎች መሰረተልማቶችና የህብረተሰቡ ሞራላዊና ስነልቦናዊ ሁኔታ ከጠረፍ በርቀት ከሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል ብዙ የተለየ እንዳይሆን አድርገዋል።

እስራኤሎችም በጎላን ሀይት ተራሮች ስርና ከሶርያ ጦር የመከላከያ ወረዳ ብዙም ሳይርቅ የሚኖረው ህዝባቸው ተገቢውና ለሁኔታው የሚመጥን የፖሊሲና የተግባር እርምጃ በመውሰዳቸው ምክንያት የህብረተሰቡ እድገት እና ያከባቢው ሁኔታ የእስራኤልና የሶርያ ጦር ሰራዊቶች ከተፋጠጡበት ራቅ ብሎ ከሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል ብዙም ያልተለዬ እንዲሆን አድርገዋል። ከነዚህ በመማር ባለፈው የአስራ ስምንት የሰላም እጦት ጊዜ ውስጥ የፌደራል መንግስትና ክልሎች ብዙ መስራት ይችሉና ተገቢም እንደነበረ፣ ችግሩም አሁን ካለበት የተሻለ ሊሆን ይችል እንደነበር መገንዘብ ከባድ አይሆንም።

## 13. አጭር ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ

በዚህ የኤርትራ አዋሳኝ በሆኑት የትግራይ እና የዓፋር አከባቢዎች ሁለት ሚልዮን (2,000,000) የሚሆን ህዝብ ከልማቱ ርቆ በሰላም እጦት እና ጭንቅ ላይ ሆኖ በድህነት አራንቋ ለሀያ አመት ዘልቋል። በሁለቱ ሀገሮች በተፈጠረው ችግር ምክንያት የነዚህ የኤርትራ አዋሳኝ አከባቢዎች ነዋሪ ህዝብ የችግሩ ቀዳሚ ሰለባ በመሆኑ ምክንያት ሊደገፍ እና ትኩረት ሊሰጠው ሲገባ ተረስቶ ቆይተዋል። ከባድ ዋጋም ከፍሏል። አሁንም ትኩረት አጥቶ ዋጋ እየከፈለ ይገኛል።

የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን ለማረጋገጥ በመንግስት የሚዘረጉ የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ህዝቦችን ተጠቃሚ ማድረግ እንዳለበት የሚታወቅ ነው:: በተለይ ደግሞ ጦርነትና ሰላም ማጣትን ጨምሮ በተለያዩ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት በድህነትና በተጋላጭነት ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ለሚዘረጉ አገልግሎቶች ተደራሽ እንዳይሆኑ የሚያግዱዋቸው በርካታ መሰናክሎች ያሉባቸው መሆኑ ደግሞ በዚሁ የኤርትራ አዋሳኝ በሆኑት አከባቢዎች የሚኖረው ህዝብ እና የገባበት የድህነት እና የሶቆቃ ኑሮ ከሚያሳየው እውነታ ሌላ የተሸለ መገለጫ ሊኖር አይችልም:: ስለሆነም መንግስት፣ ህዝቡ በጦርነቱ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ልዩ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ ይህንን ሀገራዊ፣ ውስብስበና ለአስርት አመታት የዘለቀው ችግር የተሸከመውን የህብረተሰብ ክፍል ችግሩ እንዲቃለልለና ከባሰ ብርሰት

እንዲተርፍ የሚያደርግ ልዩ ድጋፍ እና ትኩረት የመስጠት መንግስትና ክልሎች ሀላፊነትና ግዴታ አለባቸው::

ይህንን የሀገሪቱ ዜጎች እና ህዝቦችን መሰረታዊ መብት በኢ.ፌዲሪ ሕገ-መንግስት የተለያዩ አንቀጾች ላይ በግልፅ ሰፍሮ የሚገኝ ሲሆን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶችን አስመልክቶ በተለይም በአንቀጽ 41 ሥር በዝርዝር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተጨማሪ በአንቀፅ 90፤

*"የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ያደርጋል" በሚል ተደንግጓል::*

በዚህ እና በዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶች መሰረት በአከባቢው ያሉት ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለማቃለል ብያንስ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳባች መውሰድ ያስፈልጋል።

## ሀ. በኢኮኖሚ መስክ

በየዳሰሳ ጥናቱ ውጤት እንደተገለፀው የህብረተሰቡ ኑሮ በከፍተኛ ሁኔታ ስለተጎዳ ኑሮው የሚሻሻልበትና የሚያገግምበት ብያንስ የሚከተሉትን አፋጣኝ እርምጃዎች መውሰድ የስፈልጋል

- ለአስርት አመታት እንዲማቅቅ ካደረገው የማረት የስንዴ ልመናና እርዳታ የሚያላቅቅ አፋጣኝ ስራ መስራት።

- አንድ ለአምስት በሚል እስከ ጣብያ ድረስ ለልማት በሚል ሽፋን የተዘረጋውና ህብረተሰቡን ጠፍሮ የያዘው የአፈናና የጭቆና መሳርያ ከመሆን አልፎ የገጠሩም የከተማውም ህብረተሰብ በነፃነት ሰርቶ ኑሮውን እንዳያሻሽል ያደረገ አደገኛ መዋቅር ከህዝቡ እንዲነሳ በማድረግ ህዝቡ በመረጠው ሁኔታ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ።

- በሰላም እጦትና አከባቢው የጦር ካምፕ በመሆኑ ምክንያት የደረሱ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተለይተውና ተጠንተው፣ የክልሉና የፌደራል መንግስቱ ድርሻ ተለይቶ ህብረተሰቡን መደጎምና መደገፍ።

- ህብረተሰቡ የደረሰበት ጉዳት ከባድና ዘርፈ ብዙ መሆኑና አከባቢው ጭራሽ ተረስቶ የነበረ መሆኑ ግምት ውስጥ በማስገባት የመሰረተ ልማት አውታሮች የማስፋት ስራ፣ ላለፈው ጥፋት ካሳም መሆኑ ግምት ተሰጥቶት በልዩ በጀትና ትኩረት ባፋጣኝ እንዲሰራለት ማድረግ።

## ለ. ፖለቲካዊ፣ ሞራልና ስነልቦናን በሚመለከት

- ከሁሉም በፊት ህብረተሰቡን ወደ ለማኝነትና ተመፅዋዋችነት ያሸጋገረው የስንዴ ምፅዋት (ማረት ሲንድሮም) አላቆ የህዝቡን ፖለቲካዊ ነፃነት በማረጋገጥ መጀመርና ህዝባዊና ዘላቂ መፍትሄ ማድረግ።

- ህብረተሰቡን ጠፍረው የያዙት የሰብአዊና ዴሞክርያስያዊ መብት ችግሮች፣ ካለው ድህነትና የሰላም እጦት ጋር የፈጠሩት ጫና ተለይተው፣ ህገመንግስቱ ያጎናፀፈውን

መብት መነሻ ተደርጎ እንዲሻሻሉና እንዲስተካከሉ ማድረግ። ይህም በህዝቡና በህዝቡ ፍላጎት ብቻ የተቃኘ፣ ከእኔ አውቅልሀለሁ የፀዳ እንዲሆን ማድረግ።

## ሐ. የመገናኛ ብዙሀንን በሚመለከት

- የመገናኛ ብዙሀንና ጋዜጠኞች በህግ የተከለከሉ እስኪመስሉ ባለፉት 18 አመታት ወደ አከባቢውና ወደ ህብረሰቡ ዞር አላሉም። የህብረተሰቡን ድምፅ በማስተጋባት ረገድም ይህ ነው የሚባል ስራ አልሰሩም። ይህ መቀጠል የሌለበት አደገኛ ሁኔታ ስለሆነ ህዝብን ማገልገል ነው ስራችን የሚሉት መንግስትና ክልሎች የህዝቡን ችግር ለማዳመጥ፣ ሚድያዎች መሪዎችን የማጀብ ስራ ብቻ ከሚሰሩ ወደ ተመቻቸ ሁኔታና በፖሊሲ በተደገፈ አሰራርና ስምሪት ችግር ወደ አለበት አከባቢ እንዲሰማሩ ሊደረግ ይገባል። የሚሰማሩትም ሊበረታቱ ይገባል። ከምንም በላይ ፀረ ህዝብ የሆነው ደግሞ ቅድመ ምርመራ (ሳንሱር) በማድረግ ይህ የወዳጅ ይህ የጠላት ነው እያሉ የህዝብ መረጃ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት የሚፃረር አካሄድ መንግስት እና የክልሉ መስተዳደር መፍትሔ ሊያበጁለት ይገባል፡፡

## መ. ምልሻዎች በሚመለከት

- የትግራይ እና ዓፋር ምልሻዎች የመደበኛ ሰራዊት ግዳጅ ያለምንም ድጋፍ እየተሰጣቸው ግዳጁን ሲወጡ ተጎድቷል። ነፃ ሂወትና ጉልበት ሊሰጡ እየተገደዱ አስከፊ ሂወት እንዲመሩና በዛ ልክ ቤተሰቦቻቸው እንዲጎዱ ተደርጓል። ለዚህ ሁሉ ህገ ወጥ አጠቃቀም ባለቤት እንዲኖረው ተደርጎ፣ ካሳ አግኝተው ወደ ህጋዊ የምልሻ ስራ ሊመለሱ ይገባል።

ሰ. አካባቢው በሁሉም መልኩ በኢኮኖሚ በሞራል የተጎዳ መሆኑና ችግሩ መፍታት (ማቃለል) ይቅርና ችግሩ እንዲታወቅለትም ያልተደረገ መሆኑ ታሳቢ ተደርጎና አሁን ከኤርትራ ጋር የተደረሰው የሰላም ስምምነት በጣም አበረታች ሁኔታ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሆኖም ግን በጠረፍ አካባቢ ሲማቅቅ የነበረው በሚልዮኖች የሚቆጠር ህዝብ ከሌላው ከአካባቢው ራቅ ብሎ ካለው ህብረተሰብ ጋር እኩል እንዲራመድ የሚያስችሉ እርምጃዎች ሊወሰዱና ሊኖሩ ይገባል፡፡ ለዚህም መንግስት ክልሉና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በቅንጅት ትኩረት ሊሰጡት ይገባል ካልሆነ ከኤርትራ ጋር ሰላም መሆኑ በጣም ትልቅ ፋይዳ ያለው ቢሆንም የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ በልማትም ሆነ በሌላ መልኩ ወደ ኋላ መጎተቱ አይቀርም፡፡

**ማስታወሻ፡-** ይህ ዳሰሳ ወይም ጥናት በአጭር ጊዜ የተከናወነ እና በመነሻነት ያገለግላል በሚል መነሻ ያደረገ እንጂ በቂ ጊዜ እና በጀት በመመደብ ጥናቱ ቢከናወን በዚህ ጽሁፍ ከተገለጸ በተሻለ እና የበለጠ ሁኔታውን ለመረዳት የሚያስችል ግኝት ሊኖር እና ሊገኝ እንደሚችል ይታመናል፡፡